# ትግሉ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲና ለሊበራል ዲሞክራሲ በሚታገሉ መሀከል አይደለም- ችግሩ ሌላ ቦታ ላይ ነው ያለው!

## መግቢያ

የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታና የፖለቲካ አገዛዝ አስመልክቶ ባለፉት 20 ዐመታት የተለያዩ አስተያየቶች ይሰጣሉ። ሁላችንም እንደመሰለን የአገራችንን ሁኔታ እንተረጉማለን። እንደሚባለው አንድን ተጨባጭ ሁኔታና የፖለቲካ አወቃቀር እንደመተንተንና ለትግሉ ትክክለኛ አቅጣጫ እንደመስጠት ከባድ ነገር የለም ። በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተለያየ አቋም ይዘው የሚታገሉ ድርጅቶች ስለሚኖሩ ሁሉም በየፊናውና በሚመስለው መልክ አንድን ተጨባጭ ሁኔታ ይተረጉማል። ስልጣን ላይም በሚወጣበት ጊዜ ቀደም ብሎ `ሁኔታውን በተረጎመው` መሰረት ለመለወጥና ህብረተሰቡን በመሰለው መልክ ለመቅረጽና እንዲከተለው በማድረግ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚችል ይመስለዋል። በሌላ ወገን ደግሞ አንድን ተጨባጭ ሁኔታና የፖለቲካ አወቃቀር ለመተንተንና ይህንን ይመስላል ፣ ስለዚህም እኛ በሚመስለንና በምናምንበት መልክ መተካት አለበት ብሎ አንድ ወይም የተለያዩ ድርጅቶች በሚነሱበት ጊዜ ዝም ብለው አይደለም የሚታገሉት። አንድ የሚያምኑብት `ፍልስፍና` ወይም `ርዕይ` ይኖራቸዋል። ይህ ርዕይ ወይም ፍልስፍና ደግሞ የህብረተሰቡን ችግር ይፈታል ፤ ህዝቡንም ወደ ዕውነተኛ ነጻነት ሊያመራ ይችላል ተብሎ ስለሚገመት ህዝባዊ ተቀባይነት እንዲኖረው በየቀኑ ልፊፋ ይደረጋል።

ባለፉት 20 ዐመታት የወያኔን አገዛዝ ምንነት ለመግለጽ የተለያዩ አስተያየቶችና የትግል መፈክሮች ሲሰጡ ከርመዋል። ከከፋፋይነት እስከ አምባገነናዊ አገዛዝ ፣ የደቡብ አፍሪቃውን የአፓርታይድ አገዛዝ የሚመስል አገዛዝ የመሰረተና እስከ ማፊያዊ ፖለቲካ የሚያካሂድ አገዛዝ ፣ ከጋንግሰተር ካፒታሊዝም አራማጅ እስከ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ድረስ ያሰፈነ... ወዘተ. እያልን የተለያዩ ስሞች በመስጠት ለመታገል ተሞክሯል። ከነዚህ ሁሉ አይሎ የወጣውና በብዙዎቹ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ፣ የዛሬው አገዛዝ አብዮታዊ ዲሞክራሲን የሚያካሂድ ነው ፤ በህብረተሰብአችን ውስጥ ኮሙኒዝምን የሚመስል አንድ ወጥ አገዛዝ በመትከልና ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ ለብዙ ዐመታት ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚፈልግ ነው የሚለውና ፣ እኛ ደግሞ ለሊበራል ዲሞክራሲና ለነጻ ገበያ ነው የምንታገለው በሚለው መሀከል የሚደረግ ትግል ሁኖ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። ይህ ዐይነቱ የትግል ስልትና አገዛዙ ይህንን የሚመስል ባህርይ አለው ብሎ ህዝቡን ለማስተማርና ቅስቀሳ እያደረጉ `የነጻነቱን ፈለግ` ለማሳየት የሚስተጋባው ቅስቀሳ የቱን ያህል ተጨባጩን ሁኔታ የሚያንጸባርቅ እንደሆን ፣ በሳይንስ መነጽርም ሲመረመር የህዝባችንን ችግር ፈትቶ የሰለጠነችና የተከበረች ኢትዮጵያን ለመመስረት ይርዳ አይርዳ ለተከታዮችና ለሰፊው ህዝብ ግልጽ አይደለም። እንደሚታወቀው በተለያዩ አገሮች ለስልጣን የሚታገሉ ኤሊቶች ይህንን ወይም ያንን ርዕዮተ-ዓለም እንከተላለን እያሉ ቅስቀሳ በማድረግ የየህዝቦቻቸውን አመለካከት ለመሳብ ይታገላሉ። ርዕዮተ-ዓለምን ሽፋን አድርገው የሚታገሉ ድርጅቶች ወይም ፓርቲዎች ደግሞ ስልጣን ላይ በሚወጡበት ጊዜ እንዳሉትና ህዝባቸው እንደተመኘው ቃል-ኪዳን የገቡትን መሰረተ-ሀሳብ ተግባር ላይ በማዋል ነጻነት ሲያጎናጽፉት አይታይም። በዚህም ምክንያት የተነሳ በብዙ አገሮች የሚደረጉ ትግሎች ጥቂት ኤሊት ነን የሚሉና ርዕዮተ-ዓለምን ተገን በማድረግ የራሳቸውን ስሜትና ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግና በስልጣን ላይ ሆነው ህገ-መንግስቶቻቸውን በመጻረር ህዝቦቻቸውን እንደፈለጉ የሚበውዙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ለመሆኑ በዕድሜያችን የተከታተልነውና በየቀኑ በዐይናችን ስር የሚተላለፍ ሀቅ ነው። ስለዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን ምድር የሚካሄደው ትግል የፈለገውን የርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ይከናነብ ጥቂት ምሁራን ነን ፣ ሁሉንም ነገር እናውቃለን ከሚሉት አስተሳሰብና ከነሱ ጥቅም አልፎ ሊሄድ የሚችል አይደለም ፤ አይሆንምም።

ይህ ጸሀፊ የነጻ ገበያን በሚመለከትና በአገራችን ምድር ተግባራዊ የሆነውንና አገዛዙ የሚመራበትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ትክክል ነው ብሎ በሚያምንበት መልክ እየተነተነ ለማቅረብ ሞክሯል። እስከዛሬ ድረስ ግን የአጻጻፍ ስልቴንና አተናተኔን በሚመለከት ትክክል አይደለህም ብሎ አንድም ቦታ ላይ ትችት የሰጠ የለም። በአገራችን ያለው ትልቁ ችግር አንድ ህብረተሰቡን የሚመለከት ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ በዚያ ዙሪያ ውይይቱ መልክ እስኪይዝና በዚህ መልክ ችግሩን መፍታት ይቻላል ብሎ ለመታገል ክርክር ስለማይደረግ

እኔም ሆንኩ ሌላው በመሰለው መልክ ሃሳቡን ይሰነዝራል። ጥራት ያለው ትግል ከማካሄድና የህብረተሰቡን አስተሳሰብ በቀና መንፈስ ከመቅረጽ ይልቅ ውዥንብር በመንዛት የህዝብ ዕውነተኛ ነጻነት ለዝንተ-ዓለም ተንጠልጥሎ እንዲቀር ይደረጋል። በተለይም ጮሌዎችና መፈክርን እያነሱ ህዝብን የሚያደነቁሩ በቀላሉ ተቀባይነትን በሚያገኙበት በኛ ህብረተሰብ ውስጥ በሃሳብ ዙሪያ የሚደረግ ትግል ተደማጭነት አይኖረውም። እልክ በሚያሰጨርስና ራስ ምታት የሚያሲዝ ፣ እንዲያም ሲል ወደ ስም ማጥፋት ዘመቻ የተደረሰበት ከአስራ አምስት ዐመታት በላይ በማያቋርጥ የተሳተፍኩበት ትግል የሚያረጋግጠው ብዙዎቻችን ጥራት ላለው አስተሳሰብ ዝግጁ እንዳልሆንና ፣ ስልጣን ለመያዝ ብቻ ትግል የምናደርግ ነው የሚመስለው። በዚህ ዐይነቱ የትግል ዘዴ ስልጣን ለመያዝ ቢቻል እንኳ በምንም ዐይነት ህዝባችንን ስልጣኔ ለማጎናጸፍ እንደማይቻል ከምንግዜውም በላይ ለመገንዘብ የቻልኩበት ሁኔታ በጭንቅላቴ ውስጥ ተቀርጿል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ ዛሬ እንደዚሁ ይህንን ነው ለኢትዮጵያ ህዝቦች የምመኘውና ተግባራዊ ለማድረግ የምታገለው ብሎ ህዝብን ለማሳመን ይሯሯጥ ይሆናል። የሚፈተነው ግን እስካሁን የታገለለትን መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ሲችልና የህዝብን የዳቦና የዲሞክራሲ እንዲያም ሲል የአገር ግንባታን ጥያቄ ሲመልስ ወይም መሰመር ሲያሲዝ ብቻ ነው።

## የሃሳብ ጥራት አስፈላጊነት!

አንዳንድ ጊዜ ሲያመን ሀኪም ቤት ወይም ሀኪም ጋ እንሄዳለን። ሀኪም ቤት ስንሄድ ለበሽታችን ፍቱን መድሃኒት ለማግኘትና ድነን በሙሉ ጤና ስራችንን ለመስራት በመመኘት ነው። ወደ ሃኪም ቤትም የምንሄደው ራሳችንን ለማከም ዕውቀት ስለሌንና የበሽታችንን መንስዔ ለማወቅና መፍትሄ ለማግኘት ነው። በዚህም በሃኪሙ ላይ ሙሉ ዕምነት አለን ማለት ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ሃኪሙ በሽታችንን ሊፈውስ የሚችል መድሃኒት የሚያዝልን በሱ የመመርመር ችሎታ ብቻ ሳይሆን እኛም ስንተባበረው ነው። ለሚጠይቀን ጥያቄ ሁሉ ተባባሪ ስንሆንና የህይወታችንና የአኗኗራችንን ታሪክ በትክክል ዘርዝረን ከነገርነው ተቀራራቢ መድሃኒት ሊያዝልን ይችላል። አንድ ሃኪም የተማረና የሰለጠነ እንደ መሆኑ መጠንና በመሃላ ቃል-ኪዳን የገባውም ነገር ስላለ ታማሚውን ሊረዳ የሚችለው ይህንን መሰረተ-ሃሳብ የተከተለ እንደሆን ብቻ ነው። በሌላ አነጋገር በዘዴ ወይም በተማረው ስልት ብቻ ሲሰራና የታማሚውን ችግር ለመረዳት የሚያስችል ልዩ ችሎታ ሲኖረው ከበሽታው የሚፈውሰውን መድሃኒት ሊያዝለት ይችላል። ጠለቅ ወዳለ ሀተታ ሳልገባ ይህ አገላለጽ ላነሳሁት የክርክር መነሻ እንደ መተንተኛ ዘዴ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

እኛም በትግል ዓለም ውስጥ የተሰማራንና በተለይም ደግሞ በዚህም በዚያም ድምጻችንን የምናሰማና ተቀባይነት እንዲኖረን የምንጥር አንድ የአሰራር ስልትንና ፍልስፍናን በመከተል ብቻ ነው። አንድንም ሁኔታ ትክክል ይሁን አይሁን ለመተንተን የምንጥረው የምናምንበትን ፍልስፍና ወይም በትምህርት ገበታ ላይ የቀሰምነውን ዕውቀት በመመርኮዝ ነው። አጻጻፋችንና አተናተናችን ደግሞ ፣ ይህ ነው የምናምንበት የትግል ስልትና ፍልስፍና ብለን እሱን ተመርኩዘን የማንጽፍ ከሆነ ህዝብን ማደናበር ብቻ ሳይሆን ትልቅ የታሪክ ወንጀልም እንሰራለን ማለት ነው። ዝም ብሎ ለመታገል የሚደረግ ትግል የለም። በሌላ ወገን ደግሞ አንድ ነገር በጥቁርና በነጭ እንደሚገለጽ መተንተን እንደማይቻል ይህ ጸሀፊ ያውቃል። የዚህ ዐይነቱ የአጻጻፍ ስልት ለክርክር የማያመች ብቻ ሳይሆን ወደ አክራሪነት በማምራት ችግር ፈቺ ከመሆን ይልቅ የሰዎችን አስተሳሰብ በማዘበራረቅ ህብረተሰብአዊ ችግር እንዳይፈታ እንቅፋት ይሆናል። ለዚህም ይህ ጸሀፊ በተለይም አንዳንድ የግንባር ቀደምትነትን ሚና በያዙ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ ድርጅቶች የሚታተመውንና የሚነገረውን እስከዚህም ከሳይንስንና ከፍልስፍና ጋር በጥብቅ ያልተያያዘውን የአጻጻፍ ስልትና የትግል ዘዴ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን ለመፍታት የማያመች የአሰራር ስልት ነው ብሎ ያምናል። ያለፉትን የሃያ ዐመታት ጽሁፎች እያገላበጥን ብንመለከትና ትግሉም እስከዛሬ ሊንዛዛና የህብረተሰብአችንም ችግር መፍትሄ ሊያገኝ ያልቻለበት ዋናው ምክንያት ትግላችንና የምናስተጋባው መፈክር ከተጨባጩ የአገራችን ሁኔታና የፖለቲካ አወቃቀር ፣ እንዲሁም ደግሞ የውጭው ዓለም የሚያደርግብንን ጫና በሚገባ ያገናዘበና ሊተንትንም የተዘጋጀ እንዳለሆነ ማረጋገጥ ይቻላል። ይህ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በትክክል ለማንበብ ያለመቻል ወይም ደግሞ ራስ በመሰለ መልክ ለመተርጎም መሞከር የኛ ችግር ብቻ አይደለም። ፍልስፍናና ሳይንስ እንደ ተጨባጭ ሁኔታዎች መተንተኛና የሰዎች የአስተሳሰብ ስልት ማወቂያ መሳሪያዎች ሆነው ቀስ በቀስ ተቀባይነትን ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ ያለ ፣ በተለይም አንድን ተጨባጭ ሁኔታና የፖለቲካ ተዋናዮችን ባህርይና የመንግስትን አወቃቀር

ለማወቅ ምሁራንን ሰያጨቃጭቅ የነበረ አስቸጋሪ የትግል ስልት ጉዳይ ነው። በሌላ አነጋገር የፍቅር ደብዳቤና ተራ የልበ-ወለድ አጻጻፍ ካልሆነ በስተቀር በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ህብረተሰብአዊና የህሊና ቀውስ ችግር አፍጦ አግጦ በሚታይበት ጊዜ ሁኔታውን ለመግለጽ  ፈላስፋዎች ወይም ምሁሮች ትክክል ነው ብለው የተቀበሉትን ስልት ብቻ በመከተል የህብረተሰብአቸውን የችግር ምንጭ ለመረዳትና መፍትሄ ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ። በአቋማቸው ጸንተው በመቆም ተቀባይነት እንዲኖረው ለማሳመን ይሞክራሉ። በዚህም ምክንያት የሚያምኑበትንና የሚከተሉትን ወደ ውጭ በማውጣት ሳይውዱ በግድ ውይይታቸው በሃሰብ ዙሪያ እንዲያተኩር በማድረግ ተከታዮችን ለማፍራትና ቀስ በቀስም የህብረተሰቦቻቸውን ችግር መፍቻ ለማድረግ ይታገላሉ። የኛው ግን ከዚህ ለየት ይላል።

ለምሳሌ የዛሬ ሶስት ሺህ ዐመት ትግል ሲጀመር በጊዜው የነበረውን ህብረተሰብአዊ ችግር ለመረዳት ጥያቄ ያቀርቡ የነበሩ ፈላስፋዎች የችግሩን ምንጭ ለመረዳት ይጨነቁበት የነበረው የትግል ዘዴ እንዲያው በደፈናው ትግሉ በጨቋኞችና በተጨቋኞች መሀከል ያለ ችግር ነው ብለው በጥቁርና በነጭ በመሳል ሳይሆን ፣ በተለይም በስልጣን ላይ ያሉትን መሪዎች ባህርይ ለመረዳትና ፣ ምንስ ነገር ነው ወደ ጭካኔነት የሚያመራቸው ? ብለው ጥያቄ በማቅረብና መልስ ለማግኘት  ጥረት በማድረግ ነው። ይህ ችግሩን ለመረዳት መጣሪያ ዘዴ ምናልባት ለብዙዎቻችን የቅንጦትና የጥቂት ምሁሮች መዘላበጂያ መንገድ መስሎ ሊታየን ይችል ሆናል። ደግሜ ደጋግሜ ለማሳየት እንደሞከርኩት ፣ የዛሬውን የአገራችንን የተወሳሰበ ሁኔታም ሆነ የአገዛዙን የፖለቲካ ስሌት ድሮ እንደምንለው ዐይነት በጨቋኝና በተጨቋኝ መሀከል በመክፈል የችግሩን መንስዔና ባህርይ ልንተነትን አንችልም። ከዚህም ስንነሳ ትግሉ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲና ለሊበራል ዲሞክራሲ ፕሮግራሞችና እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ በሚጥሩ መሀከል የሚደረግ አይደለም። የአገራችንን ተጨባጭ የማቴሪያል ሁኔታና የፖለቲካ አወቃቀርም ሆነ የገዢውን ባህርይ በቀላሉ እንደዚህ በመግለጽ ችግሩን ልንረዳና መፍትሄ ለመስጠት አንችልም። ስለዚህም የዛሬ ሶስት ሺህ ዐመት የፈለቀው አስተሳሰብን ለማጥራትና አንድን ሁኔታ ለመረዳት የተደረሰበት የትግል ዘዴና እስከ አስራ ሰባተኛው ክፍለ-ዘመንም የዘለቀውና ሲያከራክርም የቆየበት ምክንያትና ዛሬም አፍጦ አግጦ ያለው ችግር አንድን ሁኔታ ለመረዳት በቀጥታ ከምናያቸው ነገሮች ባሻገር አልፈን ለመመርመር ጥረት ማድረግ እንዳለብን ነው። አንድ ህብረተሰብ ራሱን እንዲያውቅና ዕውነተኛውን ስልጣኔ መስርቶ በመፈቃቀር ይኖር ዘንድ የችግሩን ምንጭ በፍልስፍናና በሳይንስ መነጽር መመርመርና መረዳት ያስፈልጋል። ጦርነትና ረሃብ እንዲሁም ደግሞ ድህነት ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ እንዲወገዱና እንዲወድሙ ችግሩን የምንመረምርበት ዘዴ ትክክለኛውን መልስ ይስጠን አይስጠን እየደጋገምን መጠየቅ አለብን። ቶሎ ብለን አንድ አቋም በመያዝና ወደ ግብዝነት ማምራት ችግሩ እንዲወሳሰብ ከማድረግ ይልቅ ህዝብ የሚፈልገውን ስልጣኔ ልናመጣለት በፍጹም አንችልም። ለዚህም ነው በዚያን ጊዜ የተጀመረው ትግል እንዲያው በስልጣን ላይ የነበሩትን ገዢዎች ብቻ በማሰውገድ ችግሩ ሊፈታ እንደማይችል የተደረሰበት መደምደሚያ። ስለዚህም ይነሳና ያከራክር የነበረው ጥያቄ ምንድነው በስልጣን ያሉ ገዢዎችን አረመኔ እንዲሆኑ የሚገፋፋቸው? ለምንስ ነው ህብረተሰብአቸውን ለማተረማመስና በዘለዓለማዊ ስቃይ ውስጥ እንዲኖር የሚያደርጉት? ለምንስ ሁል ጊዜ ወደ ጦርነት ያመራሉ? ለህቦቻቸውስ ማለቅ ምክንያት ይሆናሉ ? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ጭንቅላትን የሚያስጨንቅ የመመራመሪያ ዘዴ ባይፈጠር ኖሮና ፣ እየመላለሱ ጥያቄ ባይቀርብና በተከታታዩም ትውልድ እተስፋፋና ጥራት እያገኘ ባይመጣ ኖሮ የሰው ልጅ ዕድል እንጾጦጣ ዛፍ ላይ እየዘለሉና ፍሬ እየለቀሙ እንዲሁም ደግሞ እንደቀበሮ ጉድጓድ እየማሱ መኖር በሆነ ነበር። የሰው ልጅ ግን የማሰብ ኃይል ስላለውና መሳሪያዎችንም ፈጣሪ በመሆኑ ዛሬ የምናያትን ዓለም ለመመስረት ችሏል።

ይህንን መሰረት በማድረግ ትንተና ለመስጠት ስሞክር ሶስት መሰረታዊ ጥቄያዎች ከፊቴ ድቅን ይላሉ። አንደኛው ፣ አንድ ተጨባጭ ሁኔታ የሰዎችን የኑሮአቸውንና የአስተሳሰባቸውን ሁኔታ ሊውስን ይችላል ወይ ? ወይስ ሰዎች በማሰብ ኃይላቸው የኑሮአቸውን ሁኔታ ሊለውጡ ይችላሉ ወይ? መለወጥስ ካልቻሉ የሚያግዳቸው ነገር ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ ። በመጀመሪያዎቹ በሁለቱ ጥያቄዎች መሀከል ተደጋጋፊነትና አንዱ በአንዱ ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው በጥናት የተደረሰበት ነው። በአንድ በኩል ሰዎች በማሰብ ኃይላቸው የሚኖሩበትን ሁኔታ ሊለውጡ ይችላሉ። በሌላ ወገን ደግሞ በተጨባጩ ሁኔታና በባህል ስለሚታሰሩ ወይም ስለሚታገዱ የሚኖሩበትን አስቸጋሪ ሁኔታ በትክክል ማየት እንዳይችሉ ይገደዳሉ። ሁኔታውንም ሊለውጡ አይችሉም። በዚህ ላይ ደግሞ አሁን በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ከፍተኛ የአስተሳሰብ ውዥንብር ስለሚነዛና ዕውቀት የሚባለው ነገር በተለያየ መልክ ስለሚተረጎም እንደኔ ያለ ጭንቅላቱ የተጋረደ ምስኪን

ፍጡር የጮሌ ምሁራን ሰለባ ይሆናል። ዕውነቱን ከውሸቱ ለመለየት ይሳነውና አንድ ቀን ያልፍልኛል እያለ በመጠባበቅ ወደ ዘለዓማዊ ዐለም ይሄዳል። ብዙ ሃይማኖቶች ፣ ርዕዮተ-ዓለሞችና የተለያዩ `ዕውቀቶች` በተስፋፉበት ዓለም ውስጥ ምስኪን የዓለም ህዝብ ፍዳ እንዲያይ ይደረጋል ማለት ነው። ለዚህ ነው የዛሬ ሶስት ሺህ ዐመት የጭንቅላት ትግል ሲጀመር ዕውነተኛውን መንገድ ለመፈለግና ሀቀኛውን መንገድ ለማሳሳትና የሰዎችን ስቃይ ለማራዘም ትግሉ መጧጧፍ የተጀመረው። ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የሚካሄደው ትግል ሁሉም በየፊናው ተከታይ ለማፍራትና አስተሳሰቡን እንዲያስፋፋለት ያልተቆጠበ ትግል በማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ የፈለቁት የርዕዮተ-ዓለም ውዥንብሮች ሁሉ የሰውን ጭንቅላት ለማሳሳት የሚደረጉ ወይም ደግሞ እንደ ዕምነት ተወስደው ትግል የሚደረግባቸው ዘዴዎች ናቸው። ይህ ደግሞ ህብረተሰብ ውስብብስብ እየሆነ ሲመጣና ፣ በተለይም በሀብት ክፍፍልና ክምችት ዙሪያ ግልጽ አሰላለፍ ሲታይ ጥያቄው የርዕዮተ-ዓለም ትግል እየሆነ መምጣት ቻለ። በሌላ ወገን ደግሞ ዕውነተኛ ህዝባዊ የነጻነት ትግልና ትክክለኛው የፍልስፍና ጥያቄ አነሳስ ተነጣጥለው ሊሄዱ የማይችሉ ብቻ ሳይሆኑ አንድ ህብረተሰብ የኑሮን ትርጉም ሊረዳ የሚችለው ራሱን መጠየቅ ሲችልና በማቴሪያላዊና በመንፈሳዊ መሀከል ሚዛናዊ አኗኗር ሲመሰርት ብቻ ነው። የነጻነት ጥያቄ የፍልስፍና ጥያቄ አይደለም የሚለው ኢ-ሳይንሳዊ አቀራረብ ፍልስፍናና ዕውቀት ፣ እንዲሁም ደግሞ ትክክለኛ ዕውቀት ለዕውነተኛ የህብረተሰብ ዕድገት ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለመገንዘብ ያለመቻል ነው። ዕውነተኛ ነጻነት ሊገኝ የሚችለው የሰው ልጅ የማሰብ ኃይል ሲዳብር ብቻ ነው። የማሰብ ኃይል መዳበር ደግሞ አንድን ሰው በፍላጎቱ ላይ የበላይነት እንዲኖረው ሲረዳው ፣ በዚያው መጠንም የተፈጥሮን ህግ ሊረዳ ይችላል። በሰው ልጅና በተፈጥሮ መሀከል መደጋገፍ እንዳለና እስከየትም ድረስ ብቻ በመሄድ የተፈጥሮን ሀብት መጠቀም እንደሚችል ይገነዘባል። ባጭሩ ነጻነት በመናገርና በመጻፍ እንዲሁም ደግሞ በሰላማዊ ሰልፍ ብቻ የሚገለጽ ጉዳይ አይደለም። ነጻነትን ከፍልስፍና ነጥሎ ማየት አደገኛነቱ አንድ ህዝብ የስልጣኔ ትርጉም ሁለንታዊ በሆነ መልክ እንዳይገነዘብና ጥበብ ያለው ኑሮ እንዳይመሰርት ያግደዋል። ምኞቱ ልዝንተ-ዓለም ተንጠልጥሎ እንዲቀር በማድረግ ህብረተሰብአዊ ትርምስ እንዲፈጠርና የውጭ ኃይሎች መጥተው እንዲራኮቱበት ይጋብዛል።

ወደ ተነሳሁበት ጥያቄ ላምራ። ሁል ጊዜ በፈላስፋዎችም ሆነ በህሊና-ሳይንስ ተመራማሪዎች የሚነሳው ጥያቄ ለመሆኑ ድርጊታችን ከአስተሳሰባችን ውጭ ነው ወይ? ወይስ ድርጊታችን ሁሉ በአስተሳሰባችን ነው ሊወሰን የሚችለው ? በፈላስፋዎችም ሆነ በህሊና ሳይንስም ሆነ በባህል ተመራማሪዎች የተደረሰበት መደምደሚያ ማንኛውም ሰው የሚፈጽማቸው ድርጊቶች በአእምሮው እንደሚወሰኑ ነው። ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ባህልና ዕወቀት እንዲሁም ደግሞ አስተዳደግ በሰው ልጅ የማሰብ ኃይል ላይ ተፅእኖ ይኖራቸዋል። ፍሮይድ ደግሞ የሰዎች አእምሮ በሶስት ክፍሎች እንደተከፈለና ፣ በተለይም በሁለቱ ክፍሎች መሀከል የሚደረገው ትግል የአንድን ሰው አረመኔያዊ መሆን ወይም አለመሆን ሊወስን እንደሚችል ያስተምራል። በፍሮይድ አባባል የማንኛውም ሰው አእምሮ ፣ 1ኛ) ማንኛውንም ነገር በሚያስብና ወደ ጭካኔና የራሱን ጥቅም ብቻ በማሳደድ ላይ ያተኮረ ሲሆን ፣ 2ኛው) ደግሞ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በሚኖር ኖርም ወይም ባህልና የአኗኗር ስልት የሚገዛ ነው። አስተሳሰቡ በህብረተሰቡ ውስጥ ባለውና በተለመደው የአኗኗር ስልትና ባህል ይቀረጻል። ህብረተሰቡ ማየት የማይፈልገውን እንዳያደርግ ይቆጠባል። በሌላ ወገን ደግሞ ህብረተሰብ እየተወሳሰበ ሲመጣና አንድም ሰው ካደገበት አካባቢ እየራቀ ሲሄድ የነጻነት ስሜት ስለሚሰማው የፈለገውን ማድረግ የሚችል ይመስለዋል። 3ኛው) ደግሞ ዕቅድንና ውሳኔን የሚሰጥ ክፍል ሲሆን በሁለቱ በመጀመሪያዎቹ መሀከል የሚደረገውን የማያቋርጥ ትግል ሚዛናዊ ለማድረግ ትግል ያደርጋል። ይህ የፍሮይድ አባባል ትክክል ብቻ ሳይሆን ከነፕላቶን ፍልስፍና ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ነው። በፕላቶንና የሱን ፈለግ ይዘው በተነሱ ምሁራን አስተሳሰብ የሰው ልጅ ችግር የማሰብ ኃይል ችግር ነው። ራሱን ለማግኘትና ቀናውን መንገድ ለመያዝ በዘለዓለም ትግል ውስጥ የሚኖር እንደሆን እስካሁን ድረስ ያለው የሰው ልጅ ታሪክ ያረጋግጣል። ፕላቶን ልክ እንደ ፍሮይድ አንድ በህብረተሰብ ውስጥ የተለመደ ባህልና የአኗኗር ስልት የሰውን ልጅ አስተሳሰብ ሊቀርጹ እንደሚችሉ ያስተምራል። ፕላቶን ፣ የሰው ልጅ ጭንቅላት በመጥፎና በጥሩ መልክ የተከፈለ ነው ብሎ ሲናገር ፣ የሚደረገውም ትግል ጥሩው ክፍል አይሎ እንዲወጣ በዕውነተኛ ዕውቀት መቅረጽ እንደሚያስፈልግ ያስተምራል። በሌላ ወገን ደግሞ አንድን ጭንቅላቱ ተጣሞ `የተፈጠረን` ወይም በሁኔታዎች የተበላሸን አእምሮ ማነጽ አስቸጋሪ ነው። ጥሩ ነገር እየመላለሱ ቢያስተምሩትም ጭንቅላት ውስጥ አንድ የተቀረጸ መጥፎ ነገር ስላለ በአንድ ወቅት ቀና መስሎ በሌላ ወቅት ደግሞ ነገረ-ዓለሙን ረስቶ ሰይጣን የሚሆን አለ። በዚህም ምክንያት በተለይም አንድ ዕድሜ ላይ ከደረሱ በኋላ የሰዎችን አእምሮ ማነጽ ያስቸግራል። በተለይም ማስተማርና አዕምሮአቸውን ማነጽ

የሚያስቸግረው ተማርን የሚሉ ሰዎችን ነው። ምክንያቱም አንድ ጊዜ በጭንቅላታቸው ውስጥ የተቀረጸ አሳሳች አስተሳሰብ ስላለና እሱ ብቻ ነው ትክክል ብለው ስለሚያምኑ በዚያ የተበላሻ አሳሳች ዕውቀት ህዝብ ሲሰቃይና ኑሮው ሲመሰቃቀል በፍጹም ሊገባቸው አይችልም። በትክክለኛ ዕውቀትና በቀና መንፈስ መሀከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግኑኝነት ስለማይገነዘቡ በራሳቸው ዓለም በመጠመድ ህዝብን ያሳስታሉ። ኮመን ሴንስንና ሎጂክን የህብረተሰብ ችግር መገንዘቢያና መፍቻ መሳሪያዎች አድርገው ለመጠቀም ሙከራ አያደርጉም። በዚህም ምክንያት ነው በዓለም ላይ በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ስር የሚካሄዱት ትግሎች የሰውን አስተሳሰብ የሚሸፍኑትና የሰውን ልጅ የነጻነት ጥም ፍላጎት የሚያራዝሙት።

ከዚህ ስንነሳ አንድ አስተሳሰብ በተለይም በጥሩ አናጋገር ወይም ደግሞ በግሩም የአጻጻፍ ስልት ሊሸፈን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። በተለይም ፕላቶን ሶፊስቶችን ይታገል የነበረው በሪሂቶሪክ ወይም በአነጋገር ስልት ጎበዞች ስለነበሩ የሚያዳምጣቸውን ህዝብ የማሳሳት ኃይላቸው ከፍ ያለ ነበር። ይዘት ሳይሆን ቋንቋ ወይም የአጻጻፍ ስልት እንደመመዘኛ በሆነበት ዓለም ውስጥና ቦንቦ የሚመሳሰሉ ቃላት በሚወረወሩበት ሁኔታ ውስጥ ማንኛውም ሰው የሚሰጠው አትኩሮ የጽሁፉን የአሰራር ስልትና ይዘት በመመርመር ለመመዘን ሳይሆን በስታይሉ ወይም በቋንቋው አጣጣል በመማረክ ብቻ ነው። ከዚህ ጭንቀት ለመውጣት አንድ ሰው የጻፈውን ጽሁፍ እየደጋገሙ ማንበብ ብቻ ሳይሆን ጽሁፉ ጥያቄን ሊያስነሳ የሚችል ነው ወይ? ብሎ እየደጋገሙ ጥያቄ በማቅረብና መልስ ለማግኘት ጥረት የተደረገ እንደሆን ለአንድ ችግር መፍትሄ ማግኘት ይቻላል። ከላይ እንዳልኩት የቅንጦት ሳይሆን ለህብረተሰብአችን ጥያቄና ችግር መልስ መስጠት አለብን ብለን ከተነሳን የግዴታ መከተል የሚኖርብን የትግል ፈለግ ነው። ካለበለዚያ በአለፉት አርባ ዐመት ፣ በተለይም ደግሞ ባለፈው ሃያ ዐመት እንደተደረገው ዐይነት ትግል ውሃ ቢወቅጡት...እንደሚሉት አነጋገር ይሆናል። በተጨማሪም እየመላለሱ ጥያቄ ማቅረብ ሀቀኛውን ከአታላዩ ለመለየት ያመቻል።

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ባለፉት ሃያ ዐመታት ወያኔን ለማጋለጥና ለመታገል ብዙዎቹ የተጠቀሙበት ጽንሰ-ሃሳብ መነሻው ይገባኛል። በአንድ በኩል በአገራችን ምድር በአብዮትና በሶሻሊዝም ስም ብዙ ግፍና ወንጀል ተፈጽሟል። አንዳንድ ጥሩ ነገሮችም ቢሰሩም በግፍ በተሰራው ድርጊት ስለተሸፈኑ ሰው ሁሉ የሚታየው ግፉን ነገር እንጂ ጥሩውን ሁኔታ አይደለም። በሌላ ወገን ደግሞ አንዳንዶች የዛሬውን የአገዛዙን አረመኔ የተሞላበትን ስልትና የተተራመሰ ሁኔታ በየዋህነት ብቻ በመመልከት የሚፈጽማቸውን ማንኛውንም የብልግናና አገርን የሚጎዱ ጉዳዮች በሙሉ ከአብዮትና ከሶሻሊዝም ጋር ሊያያይዙ ይሞክራሉ። በእንደዚህ ዐይነቱ አሳሳች አቀራረብና ቅስቀሳ የምናምን ከሆነ በክርስትናና በእስላም ሃይማኖት ስም መዐት ወንጀሎች ተፈጽመዋል።ዛሬም እየተፈጸሙ ነው። በዚህ መልክ ዕውነተኛ ምሁራዊ ዕውቀት ባልተስፋፋበትና ማንም እየተነሳ ያዙኝ ልቀቁኝ በሚልበት አገር ውስጥ ደግሞ ህዝብን ለማሳሳትና ዕውነቱን ከውሸቱ እንዳይለይ ማድረግ ይቻላል። አንድን ህዝብ ማፍዘዝ ይቻላል። ይህ ዐይነቱ ህዝብ አሳሳች የትግል ዘዴ ደግሞ እዚያው በዚያው በነጻ ገበያ ስም ብዙ ወንጀል እየተሰራና ራሳቸውም ታጋይ ነን ባዮች የወያኔ የነጻ ገበያ ስልት ተጠቃሚ በሆኑበት አገር ውስጥ ነው። ሌባው ከሰረቀ በኋላ ሌባ ሌባ እያሉ ሲከታተሉት ፣ እሱም ሌባ ሌባ በማለት ላለመያዝ ህዝብን እንደሚያሳስተው ዐይነት ሁኔታ ውስጥ በአገራችን ምድር እየተካሄደ ነው ማለት ነው። የሌባ ዐይነ ደረቅ... እንዲሉ! ከዚህ ስንነሳ ፣ ከዚህ አስቸጋሪና ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት እስቲ አብዮታዊ ዲሞክራሲና ሊበራል ዲሞክራሲ የሚሉትን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናኘት እንወያይባቸው።

## ወያኔ አብዮታዊ ዲሞክራት ወይስ ሌላ !

በህብረተሰብ ሳይንስ ምሁሮች ፣ በፈላስፎችና በታሪክ ተመራማሪዎች አንድ የተደረሰበት መግባቢያ አንድን ህብረተሰብ ለመረዳት የቆሙበትን የማቴሪያልና የሚገዙበትን የማሰብ ኃይል ለመመርመር የግዴታ ከየአገሮቹ ሁኔታ መነሳት እንደሚያስፈልግ ነው። በሌላ አነጋገር ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ይህን ነኝ ቢልም የመጨረሻ መጨረሻ የሚሰራቸው ስራዎች ፣ አስተሳሰቦችና የጊዜ አጠቃቀሞች በእዚያው ተወልዶ ባደገበትና እንደባህል ከሰውነቱ ጋር ባዋሃደው ነው ሊወሰን የሚችለው። በሌላ ወገን ግን ባለፉት ስድሳ ዐመታት ተቀባይነትን ያገኘና እኛንም ያሳሳተ የአጻጻፍ ስልትና የአሰራር ሁኔታ አለ።

ይኸውም ከዘርና ከቀለም እንዲሁም ከህብረተሰብ አወቃቀርና ባህል ባሻገር የሰው ልጅ ፍላጎት ሁሉ አንድ ነው ፤ ሁሉም ወደዚያ ነው የሚያመራው የሚለው በኢምፔሪሲስቶች ወይም ዛሬ በግልጽ የሚታወቀው በኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም አራማጆች የሚሰበከው ሰበካ ነው። ስለሆነም ዓለም በሁለት የተከፈለች ነበረች። አንደኛው አክስሚል ፤ ዛሬ ያለን አማራጭ በዚህ ዛሬ ዓለምን በሚያሽከረክረው አንድ ተቀባይነትን ባገኘ የነጻ ገበያ ርዕዮተ-ዓለም መመራት ብቻ ነው የሚል ነው። የዛሬው የወያኔ/ኢህአዴግ አመራር ባረጀው የሶሻሊሽት ርዕዮተ-ዓለም የሚመራና የጠቅላላውን ህዝባችንን አስተሳሰብ በዚህ ለማነጽ የሚታገል ስለሆነ ይህንን ግለሰብአዊ ነጻነትን አፋኝ አገዛዝ ማሳጣትና መታገል ያስፈልጋል የሚል የአገራችንን የተወሳሳበ ሁኔታ በጥቁርና በነጭ በመሳልና በመክፈል የሁኔታዎችን ውስብስብነት ብቻ ሳይሆን የኛንም ምንነት በቅጡ እንዳንረዳና ለነጻነት እንዳንታገል የሚያግድ አደገኛ ጎዞ ነው የተያዘው። የምዕራቡን የሶስት ሺህ ዐመት የህብረተሰብ ታሪክንና በፍልስፍናም ሆነ በርዕዮተ-ዓለም ደረጃ የተካሄደውን ትግል ስንመለከት ነገሮች እንደዚህ በቁንጽል መልክ በጥቁርና በነጭ መሀከል የሚታዩና ሊተነተኑ እንደማይችሉ ነው። ግራ ቢገባኝ ይህ ሶሻሊዝም ወይም አብዮት እየተባለ ብዙ ሲሰበክበትና በዛሬው ዓለም የተጠላን ርዕዮተ-ዓለም ምንድነው ብዬ አንዳንድ ጽሁፎችን ሳነብ ፣ የሶሻሊዝም ወይም የአብዮት ጽንሰ-ሃሳብ አፍላቂዎች ዕውቀት ከምዕራቡ የህብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ብቻ ሳይሆን ፣ ምሁራኑ ራሳቸው ከሌላ አንጻር እንደዚሁ የተወሳሰበና የጠለቀ ዕውቀት እንደነበራቸው ነው መገንዘብ የሚቻለው። በተጨማሪም ይህንን አርማ ይዘው ይታገሉ የነበሩ ኃይሎች የተለያየ አመለካከትና አተረጓጎምም እንደነበራቸው ነው። ለሶሻሊዝም ይታገሉ የነበሩ ኃይሎች ሁሉ አንድ አመለካከት ነበራቸው ብሎ መጻፍም ሆነ ማውራት ትልቅ የታሪክ ወንጀል እንደመስራት ይቆጠራል። በሌላ ወገን ግን ይህ ቲዎሪ ተግባራዊ የተደረጉባቸው አገሮች ባላደጉ ወይም የማቴሪያልና የህሊና አስተሳሰባቸው ገፍቶ ባልሄደበት አገሮች ውስጥ ነው። የአሰተሳሰብ ግጭት ባላደገባቸውና ፍልስፍና እንደ ዕውቀት መነሻ ተደርጎ ባልተወሰደባቸው ኋላ-ቀሩ በሚባሉ አገሮች ነው። ከዚህ ስንነሳ የሚቀርበው ጥያቄ የሶሻሊሰት አብዮት ቲዎሪው በፈለቀበት አገር ቢካሄድ ኖሮ ውጤቱ ምን ይመስል ነበር? የተለየ ነገር ያደርጉ ነበር ወይ? ዲሞክራቶችና የሌላውን ሃሳብ ተቀባይ ይሆኑ ነበር ወይ? በእርግጠኝነት መናገር በፍጹም አይቻልም። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ግን በስታሊን አገዛዝ የተፈጸመው አሰቃቂ ድርጊትና የወሬ ወሬ የሰማነውና ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ዓለም `ለሁለት መከፈሏ` የነገሮችን ሂደት እጅግ በጠባቡ እንድንመለከት አስገድዶናል። የምዕራቡ ካፒታሊዝም የሰራውን ወንጀል ለመሸፈን በሚነዛው ፕሮፖጋንዳ ተጠምደን የየህብረተሰቦችን አስቸጋሪ የዕድገት ጉዞና ሁኔታ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ቆም በማለት እራሳችንን እንዳንጠይቅ ተገደናል። ይህ ዐይነቱ ጭፍን አመለካከት ደግሞ እኛ አንድ ቀን በአንዳች አጋጣሚ ስልጣን ብንይዝ እንኳ በሌላ መልክ የታሪክን ሂደትና የህብረተሰብን አገነባብ ከማጣመም በፍጹም ልናመልጥ አንችልም። ምክንያቱም ታሪክንና የህብረተሰብን የዕድገት ሁኔታ ሳያገናዝቡ ተግባራዊ የሚሆኑ ፖሊሲዎች በሙሉ ወደ ጥፋትና ህብረተሰብአዊ መዘበራረቅ ስለሚያመሩ ነው።

ወደ አገራችን ስንመጣ ያለው ችግርም የኛን ህብረተሰብ አወቃቃርና በየብሄረ-ሰቡ ውስጥ ያለውን የተለያየ አስተሳሰብ ለመገምገምና ከዚያ ተነስተን የፖለቲካ ተወናይ ነን ባዮችን ባህርይና ተግባር ለመረዳት ያለመቻል ነው። ይህ የሚያረጋግጠው ፣ እንደ ምዕራቡ ምሁራን -ከኒዎ-ሊበራል ውጭ ያሉ- ነገሮችን ከሁሉም አንጻር ለመመርመር ገቱ እንደሌለን ነው። የሚታየን ውጤቱና ቶሎ ቶሎ ብሎ አንድ ነገር ላይ ለመድረስ ነው። ስለሆነም ነገሮችን እኛ በምንፈልጋቸውና የዓለምን ህዝብ ባደነቆረው ፕረፖጋንዳ በመጠመድ የዛሬውን ሁኔታ ይህንን ይመስላል ብለን አንዳች መደምደሚያ ላይ እንድንደረስ ተገደናል። በሌላ ወገን ግን በፖለቲካ ዐለም ውስጥ ባልተሳተፈውና በአብዛኛው ህዝባችን ይህ ዐይነት አስተሳሰብ ቢሰፍን በፍጹም አይደንቀኝም። ምክንያቱም በአብዮት ፈንታ ደም ሲፈስ ሲያይ ፣ አገር በመገንባት ፈንታ ህብረተሰብአዊ ምስቅልቅልና እርስ በርስ መነታኮር ሲመለከት ፣ ልጆቹና ዘመድ አዝማዶቹ ስውር ሲሉበት ... ወዘተ. የሚጠይቀው ጥያቄ ሶሻሊዝምና አብዮት ማለት ይህ ነው ወይ? ብሎ ነው። እኔም እንደ የዋሁ ህዝባችን እንደዚህ ዐይነት ህብረተሰብን ደም የሚያቃባና አገርን የሚያፈራርስ ርዕዮተ-ዓለም በአፍንጫዬ ይውጣ እላለሁ። ፍቅርንና ሰላምን አስፍኖ ለአገር ግንባታ የማይጋብዝ ርዕዮተ-ዓለምን ማየት አልፈልግም እላለሁ። ጉዳዩ በእኔና በየዋሁ ህዝባችን ዘንድ እንደዚህ በቀላሉ የሚታይ ቢሆንም ከበስተጀርባው ያለውን ችግር ስንመለከት ልንገነዘበውና ልንረዳ የማንችለው ነገር እንዳለ ማንበብ ይቻላል። የብዞዎቻችንም ችግር ይህንን ከአፍንጫ ርቆ በመሄድ በአገራችን ውስጥ የሰፈነውን የባህል ትርምስና የህሊና አወቃቀር ለመመርመር ያለመቻል ነው። በተጨማሪም ለምን ተማርኩ በሚለው ፣ ወታደሩንም ጨምሮ እንደዚህ ዐይነቱ ጭካኔ በአገራችን ምድር ሊከሰት ቻለ? ብሎ ለመጠየቅ አለመቃጣት የነገሩን ሂደት በቁንጽል እንድንመለከተው አስገድዶናል።

በመሰረቱ አብዮት ማለት መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት መታገል ማለት ነው። በአንዳች ዐይነት መልክ ከአንድ ወደ ኋላ-ቀር ሁኔታ ወደ `ተሻለ ሁኔታ` ለመሸጋገር መሞከር ነው። በሌላ ወገን ደግሞ መጀመሪያ እንደዚያ የሚወደስለትና በናፍቆት የሚጠባበቁት ነገር ወደ ተግባር ሲመነዘር መዘዝ ይዞ ይመጣል። ወደ ደም መፋሰስ ያመራል። ይህ ዐይነቱ ሂደት የተፈጥሮንና የህብረተሰብ ዕድገትን ታሪክ የሚጥስ በመሆኑ መሪዎችም ሆነ ህዝቦች ወደ ፈለጉት ሶሻሊስታዊ ስርዓት ሊመጡ አይችሉም። ያም ሆነ ይህ መሰረተ-ሃሳቡ ሀብት ለሁሉም እንደ ችሎታውና እንደ አስተዋጽዎው በእኩልነት ሊከፋፈል የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚቃጣ ነው። ለዚህ ደግሞ የግዴታ የማቴሪያል ሁኔታዎች መሻሻል አለባቸው። በቲዎሪው መሰረት በገበያ ላይ በአቅራቢና በጠያቂ መሀከል የሚደረግ የዕቃና የገንዘብ ልውውጥ እንዲኖር ባይፈቅድምና ዋጋም አስተዳዳሪያዊ በሆነ መልክ ቢደነገግም የምርት ማምረቻ መሳሪያዎችን መሻሻል ግን ፍልስፍናው አይቃወምም። የገበያ ላይ ልውውጥም በፍጹም አይኖርም ማለት አይደለም። ቲዎሪው ተግባራዊ በሆነባቸው አገሮች የተደረሰበትም መደምደሚያ የቀደሙ የካፒታሊስት አገሮችን በአንዳች እምርታ ከኋላ ለመያዝና ለመወዳደር `በሶሻሊስት የሀብት ክምችት ዘዴ`(Socialist primitive accumulation) ሰፊውን ህዝብ በማንቀሳቀስ ዕድገት ለማምጣታት ይቻላል የሚለውንም በጭንቅላት በመቋጠርና በመንደፍ ነው። ቲዎሪው ተግባራዊ በተደረገባቸው አገሮች ፣ ከሶቭየት ህብረት አንስቶ እስከቻይናና ሌሎች የምስራቅ አውሮፓ አገሮችም የታየው የማቴሪያል ዕድገትን በንጹህ ጭንቅላት ለተመለከተው እነዚህ አገሮች በዚያን ጊዜ ከነበሩበት ሁኔታ ለመውጣት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም ወደ ሚለው መደምደሚያ ይወስደናል። በሌላ ወገን ደግሞ እነዚህ አገሮች በዚያን ጊዜ የካፒታሊስቱንና የነጻ ገበያውን መንገድ ቢከተሉ ኖሮ ህዝቦቻቸውን መመገብ ይችሉ ነበር ወይ? የምርት ኃይሎችንም ወይም መሳሪያዎችን ማሻሻል ይችሉ ነበር ወይ? ለመሆኑስ ይህንን ለያራምድ የሚችል የህብረተሰብ ኃይል ነበራቸው ወይ? በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። አንድ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ነገር የመንግስትን ድጋፍ ተገን አድርገው የኢኮኖሚ ዕድገትን ከተጎናጸፉት አገሮች ፣ ከነደቡብ ኮሪያ ፣ ታይዋንና ሲንጋፖር እንዲሁም አንዳንድ አገሮች በስተቀር የነፃ ገበያን ኢኮኖሚ ፍልስፍናና የእነ አይ ኤም ኤፍንና ዓለም ባንክን ምክር የተቀበሉ ብዙ የአፍሪቃና የአሺያ አገሮች በዕድገታቸው እስከዚህም ፈቀቅ እንዳላሉና ከጥገኝነት እንዳልተላቀቁ ነው የምንመለከተው። ይህ ከሆነ የምሁራን ተግባር ሁኔታዎችን ጠጋ ብሎ ከመመርመርና ህዝብን ከማስተማር ይልቅ ለምን በጥቁርና በነጭ እየተለየ ልፈፋ በማድረግ ብዞዎችን ግራ ለማጋባት ይሞከራል? ለምንስ በተወሰኑ አገሮች ብቻ የኢኮኖሚ ዕድገትና አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ እምርታ ሲታይ በሌሎች አገሮች እንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ሊፈጠር አልቻለም ? ብሎ መጠየቅ የምሁሮች ተግባር መሆን ያለበት ይመስለኛል። ጥያቄ ማቅረብና መልስ ለማግኘት መሞከር ከግብዝነት ያድነናል።

ከዚህ እጅግ የተወሳሰበ ሁኔታ ተነስተን ወደ ጥቅሉ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጽንሰ-ሃሳብ ስንመጣ ፣ በተግባር እንደታየው ፣ በሶቭየት ህብረትም ሆነ በሌሎች የሶሻሊስት አገሮች የወዛደሩ አምባገነንነት ሳይሆን የንዑስ ከበርቴው ወይም የኤሊት አምባገነንነት እንደሰፈነ አንዳንድ ምሁራን ያስረዳሉ።- *የወዛደሩ አምባገነንነት ይስፈን ማለቴ አይደለም-* በነጻ አለመደራጀት ብቻ ሳይሆን ሃሳብን በነጻ ማንሸራሸርና ጥያቄ መጠየቅ የማይቻልበት ሁኔታ በመፍጠር የጠቅላለውን ህዝብ የመፍጠር ችሎታ እንዳፈነ የማይታበል ሀቅ ነው። በተጨማሪም በየአገሮች የተዋቀረው የጸጥታ ኃይል ሰውን አላፈናፍን እንዳለና የዲሞክራሲን ጥያቄ የሚያነሱትን እስር ቤት እንዲወረወሩ ያደረገ ሁኔታ እንደተፈጠረ እንመለከታለን። እንደዚህ ዐይነቱ ስርዓት በሶሻሊስት ቲዎሪ ላይ የተመሰረተ ነው ወይ? ወይስ የየአገሮቹ የማቴሪያልና የባህል ሁኔታ የፈጠረው ነው ወይ ? ብሎ ጥያቄ ማቅረብ እንደሚገባ የባህልና የታሪክ ተመራማሪዎች ያስገነዝባሉ። እንደሚባለውም የረዥም ጊዜ የባህልና የምሁራዊ እንቅስቃሴ ባልታዩባቸው አገሮች በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ስም የሚካሄዱት ትግሎች የግዴታ ወደ አመጽና ወደ አምባገነንነት እንደሚያመሩ ነው። በተለይም የተገለጸለት ከበርቴያዊ ኃይል በሌለበት አገርና የህሊናና የባህል ተሀድሶ ባልታዩባቸው አገሮች አንዳንድ ድርጅቶችና ግለሰቦች ህብረተሰብአዊ ድክመትን በመገንዘብ የራሳቸውን ህልም ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚችሉ ነው። ባጭሩ የሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለም የፈጠረው ችግር ሳይሆን የየአገሮች ከረዥም ጊዜ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሌላን ሃሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ ያለመሆን ባህል በጭንቅላት ውስጥ መቀረጽና ይህ አማራጭ የሌለው ስርዓት ተደርጎ መወሰዱ ነው። የሰርዓት ችግር ቢሆን ኖሮ ፋሺዝም በጀርመን ምድር ባልተነሳ ነበር።አሜሪካ ጃፓንን በቦንብ ደብድባ ለብዙ ሺህ ህዝብ ዕልቂት ተጠያቂ ባልሆነች ነበር። በቬትናም ህዝብ ላይ የደረሰው የቦንብ ስርጭትና እስከዛሬ ድረስ መዘዙ ያላለቀው በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ በተጠነሰሰ ስልትና በተሰራ ቦንብ ነው ምስኪን ህዝብ ሊጨፈጨፍ የቻለው። በኢራክና

በምስኪኑ የአፍጋኒስታን ህዝብ ላይ የሚወርደውም ቦምብ በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ሰም በሚካሄድ ኃይልንና በማቴሪያል መበልጸግን ባዋህደ ታሪክን በማጣመም የሚካሂድ የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ነው። ሁለትና ሶሶት ሽብርተኛ ወይም እንደ ሳዳም ሁሴን የመሰለውን አምባገነን ገዢ ለመያዝ ሲባል በጠቅላላው ህዝብ ላይ ጦርነት አውጆ የታሪክን ቅርጽና ባህል ማውደምና እንዲሁም የተራውን ህዝብ ኑሮ ማፈራረስ አስፈላጊ አልነበረም።

ወደ ኢትዮጵያችንም ስንመጣ ያለው ችግር እነ አቶ መለስ አብዮታዊ ዲሞክራቶች ነን ስላሉ ፣ እነሱ እነከተላለን በሚሉትና በተጨባጭ የሚታየው ሁኔታ የሰማይና የመሬትን ያህል የተራራቀ ለመሆኑ ብዙ ያልተመራመረ እንኳ ሊገነዘበው ይችላል። በእርግጥስ የእነ አቶ መለስ ፓርቲ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በሚለው መርህ ላይ የተመረኮዘ ነው? ያምኑበታልስ ወይ? ወይስ የነሱ ድርጊትና የፓርቲ አወቃቀር የህብረተሰብአችን የባህልና የማቴሪያል ሁኔታ ነጸብራቅ ነው ወይ? የእነ አቶ መለስና የግብረ-አበሮቻቸው ፍልስፍናና ተግባር በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ የሚወሰን ነው የምንል ከሆነ ለምንስ ከአስራ-ዘጠኝ ዐመት ጀምሮ በአይ ኤም ኤፍ የወጣውን የነጻ ገበያ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ በቁ? ለምንስ የምዕራቡ ካፒታሊስት ዐለም እሹሩሩ ብሎ ሃያ ዐመት ያህል አቅፎአቸው የምትሰሩት ስራ ሁሉ ትክክል ነው እያለ አብሮአቸው ይጓዛል? በእነሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስለተማረከና ስለረካ? ወይስ የምዕራቡ ዓለም በሚፈልገው መልክ እነ አቶ መለስ ህዝባችንን ስለሚያመሰቃቅሉና የድህነት ዘመኑን አርዝመው አቅመ-ቢስ ሲያደርጉት በዚህ ስለረካና የኢትዮጵያችንንም ዕድገት በነዚህ ኃይሎች አማካይነት ብቻ መግታት ይቻላል ብሎ ሰላመነ ነው ወይ? ክቡራትንና ክቡራንን የሊበራል ዲሞክራሲንና የነጻ ገበያን አራማጆችን በክብር የምጠይቀው እነዚህን ጥያቄዎች እንድትመልሱልኝ ነው። መልሱን በጉጉት እጠባበቃለሁ።

እኔ ግን የምነሳው ከረቀቀ ወይም ከአብስትራክት ነገር አይደለም። የማነሳው ጥያቄ የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዴት ነው የማነበው? ስልጣንና የመንግስቱ መኪና እንዴት ነው የተዋቀሩት? የአገሪቱን ሀብትስ ማንነው የሚቆጣጠረው? የሀብትስ ክፍፍል ምን ይመስላል? በማለት ተራ ጥያቄ በማንሳት ነው። ከዚህም በመነሳት ነው የፖለቲካ ትግል ስትራቴጂና የነጻነቱን ትግል ስልት መንደፍ ይቻላል ብዬ የማምነው። ስለሆነም በእኔ እምነት ዛሬ በአገራችን የሰፈነው አገዛዝና የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሶቭየት ህብረትና ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ከ 1989 እ.አ ከሚከተሉት ጋር ሲወዳደር በምንም መልኩ ለውድድር የሚቀርብ አይደለም። በንጹህ የምሁር ጭንቅላት ለተገነዘበው የድሮዎቹ ሶሻሊስት አገሮች ፖሊሲ አነሰም በዛም ህዝባዊ ባህርይ ነበረው። በአጣቃላይ ሲታይ በባህልና በስፖርት የገፋ እንደነበሩ የማይታበል ሀቅ ነው። በአንጻሩ ግን የዛሬው የወያኔ/የኢህአዴግ አገዛዝ በማቴሪያልም ሆነ በምሁርና በባህል ሁኔታ እጅግ ከተጎሳቆለና ከደቀቀ ህብረተሰብ የፈለቀ በመሆኑ ፍልስፍናውና ተግባሩ ይህንን ሁኔታ የሚያንጸባርቅ እንጂ አብዮታዊ ወይም ሶሻሊስታዊ የሚያሰኘውና ሊያረጋግጥበት የሚችልበት ሁኔታ በፍጹም የለም። የወያኔ ጽንሰትና ውልደት እንዲሁም ዕድገት የፊዩዳል ኢትዮጵያ ሁኔታ ነጸብራቅ ነው።ችኮነቱ ፣ ተንኮሉ ፣ ከፋፋይነቱና በህዝብ ላይ መባለጉና የአገርን ብሄራዊ-ነፃነት ማስገርሰሱ ከአገራችን የማቴሪያልና የህሊና ሁኔታ ተነጥሎ ሊታይ በፍጹም አይችልም። በዚህም ምክንያት በቴክኖሎጂና በሳይንስ እንዲሁም በምሁር ደረጃ መነጠቅኹኝ የሚለው የምዕራቡ ዓለም ይህንን ሁኔታ በመጠቀም እንደዚህ ዐይነቱን ኋላ-ቀር አገዛዝ መሳሪያ በማድረግ ጦርነት ቀስቃሽና ድህነትን ፈልፋይ በማድረግ ይጠቀምበታል። ለዚህም ነው የምዕራቡ ዓለም እነ አቶ መለስን እሹሩሩ እያለ የሚንከባከባቸውና በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ የሚያፈስላቸው። አንዳንድ የበሰሉና ሰብአዊነት የተዋሃዳቸው የአውሮፓና የአሜሪካ ምሁራን እንደሚሉት ፣ የምዕራቡና የአሜሪካ ካፒታሊስት አገሮች በምንም ዐይነት የደቡብ ኮሪያ ፣ የጃፓንና ዛሬ ደግሞ የቻይና ሁኔታ በአፍሪቃ ምድር እንዲደገም አይፈልጉም። ሰለዚህም በነፃ ገበያ ስም አሳበው እንደዚህ ዐይነቱን አመጸኛ አገዛዝ እየተጠቀሙ ህብረተሰብን ያመሰቃቅላሉ። ለኛ የሊበራል ዲሞክራሲና የነፃ ገበያ አራማጅ ኢትዮጵያውያን ይህ የምዕራቡ ዓለም ተንኮል በፍጹም አይታየንም። አይዋጥልንም። ምክንያቱም የፈረንጅን የበላይነትና አምላክነት አምነን ተቀብለናልና። ጥቁር የተረገመ ፣ ነጭ ደግሞ እግዚአብሄር የባረከው ነው ብለን አምነን ስለተቀበልን የሚፈጸምብንን ተንኮል ለማየት እንዳንችል ተጋርደናል። እንደዚህ ስል ነጭ ሁሉ እንደዚህ ያስባል ለማለት አይደለም። ከአስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ እየበለጸገ የመጣው የምዕራቡ ዓለም አፍሪቃን የሚመለከትበት መነጽርና የማጥቃት ሁኔታ ግልጽ ከሆነ ወደ ረቀቀ ሁኔታ በመሸጋገር ለብዙዎቻችን ግልጽ ያልሆነ አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮብናል። በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ስም ዓለምን በማወናበድ የስልጣኔውን መንገድ አጨልሞብናል። ስለሆነም የምናየውና የምናነበው

የዓለም ሁኔታ በጥቁርና በነጭ መሀከል እንደሚገለጽ እንጂ ውስብስቡ ዓለም ወስጥ ገብተን በመመርመር አይደለም።

ከዚህ እጅግ ከተወናበደ ሁኔታ ስንነሳ የዛሬው የኢትዮጵያ አገዛዝ በተወሰነ የአመጽ ሎጂክ ውስጥ የሚንቀሳቀስና ሀብትን የሚዘርፍና የሚያካብት ነው። አንዳንዶች ደግሞ ልዩ ዐይነት የንዑስ ከብርቴው ፋሺዝም ሰፍኗል ይላሉ። የጸጥታ ኃይል እየተባለ የሚቆላመጠውና የመንግስቱ አወቃቀር ይህንን የህብረተሰብ ሀብት እየገፈፈ በሚያካብትና ንብረትን ለውጭ ከበርቴዎች የሚሸጥን የወያኔን አገዛዝ ለመጠበቅ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ደራሽ ነጋዴዎችንና በዕውቀት ያልበሰሉትና በየሚኒስተሩና በየአገሪቱ ግዛቶች ውስጥ የተሰገሰጉትን ተገን በማድረግ ልዩ ዐይነት ዕድገትንና ስልጣኔን የሚቀናቀን አገዛዝ የመሰረተ ነው። የሀብት ቁጥጥርና ክፍፍልም በቀጥታ ከዚህ ዐይነቱ መንግስታዊ አወቃቀር ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም ምክንያት ነው በአገራችን ውስጥ በአንድ በኩል በሀብት መባለግ በሌላ በኩል ደግሞ ድህነትና ረሃብ ሰፍነው የሚታዩት። ስለሆነም በሀብት የባለጉ አዲስ መጤዎች ለአንድ የፈረንሳይ ጠርሙስ ኮኛክ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ(250 000)የኢትዮጵያ ብር እየከፈሉ የሚጠጡባትና የሚሳከሩበት አገር ናት ውድ እናት አገራችን የሆነችው። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ህዝባችን ወደ ሁለተኛ ዜግነት የተቀየረበትና በኑሮ ወድነት የሚሰቃይበት አገር ነች። ብሄራዊ ነጻነታችን በከፍተኛ ደረጃ ተገርስሷል። አገዛዙ የአሜሪካንን ቡራኬ ለማግኘት ሲል በንጹህ የሱማሌ ህዝብ ላይ በአክራሪ እስላምና በቴሮሪዝም ስም እያሳበበ የውክልና ጦርነት የሚያካሂድባት አገር ነች። የወያኔ አገዛዝ በከፍተኛ ደረጃ በምዕራቡና በአሜሪካን የስለላ ድርጅቶች በመታቀፍና በመረዳት ህዝባችንን አፍኖ የያዘ ነው። ይህ ዐይነቱ የውጭ አሽከርነትና እኔ ከሄድኩ ኢትዮጵያ ትፈራርሳለች የሚለው አነጋገር ከአብዮታዊ ዲሞክራሲና ከሶሻሊዝም መሰረተ-ሃሳብ ጋር በፍጹም ሊጣጣም አይችልም። በአንጻሩ ግን የሶሻሊስት አገር ተብለው የሚጠሩት ሶቭየት ህብረትና ሌሎች የምስራቅ አውሮፓ አገሮች ወደ ኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ እስከተሸጋገሩ ድረስ ህዝቦቻቸው በድህነትና በረሃብ ሲሰቃዩ ተሰምቶ አይታወቅም። አገራችውን አስከብረው የሚኖሩ ነበሩ። ለምን ታዲያ ስርዓቱ ፈራረሰ ? ተብሎ ጥያቄ ቢቀርብ በቀላሉ መልስ መስጠት የሚችል ያለ አይመስለኝም። በነጻ ገበያ አለመኖር ነው ብሎ ተራ መልስ ለመስጠት መሞከር ችግሩን ለመረዳት አያስችለንም። ያም ሆነ ይህ ሌላው ቢቀር የሶሻሊስት ናፍቆት የሌላቸውና ሰቭየት ህብረትና ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ይማሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያኖች እንደሚመሰክሩትና እንደሚያረጋግጡት ድህነትና ረሃብን በፍጹም እንዳላዩና ህዘቡም በነበረው ሁኔታ እስከዚህም እንደማያማርር ነው። ከብዙዎች አፍ ውስጥ እንደሰማሁት ፣ በተለይም ሰቭየት ህብረትን የሚጠላና የሚያማርር እዚያ የተማረ አንድም ኢትዮጵያዊ አላጋጠመኝም። ለማለት የምፈልገው ፣ ሶሻሊዝም ያስፈልጋል አያሰፈልግም የሚል ክርክር ውስጥ ለመግባትና የሶሻሊዝም ናፍቆት ስላለኝ ሳይሆን ፣ የምናካሂዳው የትግል ቅስቀሳና አጋዛዙን የምንሰጠው ስም ከኢትዮጵያ ተጨበጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ብቻ ሳይሆን በምንም ዐይነት ሳይንሳዊ ቲዎሪ ሊደገፍ የሚችል አይደለም። እንደዚህ ነው ብለን የምናረጋግጥበት ሳይንስ ወይም ቲዎሪ ከሌለን ደግሞ ዝም ብለን ነው የምናወራውና ስንትና ስንት ሚሊዮንን ህዝብ የምናሳስተው። አገርን ለመገንባት መታገል ዕድር እንደመመስረት አይደለም። ለአገር ግንባታ የሚታገሉ ኃይሎች የሚመረኮዙበት ቲዎሪ ወይም ፍልስፍና ያሰፈልጋቸዋል። ችግሮችን ለመረዳት በየጊዜው ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው። በጥላቻ ብቻ ተነሳስተን የምንታገል ከሆነ ደግሞ ህዝባችንን አንጠቅምም ፤ አገርም መገንባት አንችልም።

ከኢኮኖሚ አንጻር ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ለማሳየት እንደሞከርኩት ፣ አገዛዙ የሚመራበት ፖሊሲ አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ሀብትን የሚፈጥር ፖሊሲ አይደለም። ኢህአዴግ እከተላለሁ የሚለው በእርሻ ላይ የተመረኮዘ የኢንዱስትሪ ፖሊሲና ተቃዋሚውን የሚያከራክረው ነጥብ በእርግጥም ኢህአዴግ ይህንን ፖሊሲ በመከተሉ ሳይሆን ያለው ችግር ራሱ አገዛዙ የሚከተለውን ፖሊሲ እንኳ ምን እንደሆን ለመገንዘብ ያልቻለበት ሁኔታ ነው የሚታየው። የአገዛዙ ችግር የኢኮኖሚ ቲዎሪንና የፖሊሲ ልዩነቶችን ልዩነት ያለማወቁ ብቻ ሳይሆን አንድ ህብረተሰብ እንዴት እንደሚገነባ የተገነዘበ አይደለም። የውጭ ኤክስፐርቶች እጁን እየያዙ ህግና ፖሊሲ የሚያወጡለት አገዛዝ ነው በአገራችን ምድር የሰፈነው። በተለይም የፋይናንስ ሚኒስተሩ የእነ አይ ኤም ኤፍን ትዕዛዝ የሚቀበልና እንደአሽከር ታዛዥ የሆነ ለመሆኑ ፖሊሲውንም ሆነ ፎቶዎችን ለተመለከተ በቀላሉ ሊረዳ ይችላል። ከአንዳንድ ካድሬዎች እንደሚሰማው ኢትዮጵያን የምንፈልጋት ንግድ ለመነገድና ለራሳችን ሀብት ለማካበት እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም እየተባለ ነው። የመሪዎችም ዋና አላማና የሚኒስተሮችም ተግባር በሞነቴሪና በፊስካል ቲዎሪ እያሉ ህዝብን በማደናበር ሀብት እንዴት አድርገው በማካበት ከውጭ ኃይሎች ጋር በመቆላለፍ የድህነቱን ዘመን ለማራዘምና የህብረተሰቡን ድቅት ለማፋጠን የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። የኢኮኖሚው ዝብርቅርቅነት ፣

በዕቅድ አለመስራት ፣ በካፒታሊስታዊ ሎጂክ ላይ የተመሰረተ ወድድር አለመኖር ፣ በምርምርና በሳይንስ ያልተደገፈ ፖሊሲ መከተል ፣ የአገሪቱን ገበያ ከውጭ ለሚመጣ ምርት ክፍት ማድረግና ወደ ውስጥ ደግሞ የማምረት ኃይልን ማዳከም ፣ ቴክኖሎጂያዊ ምጥቀት እንዳይኖር ማገድና እርስ በርሱ የተያያዘ የስራ ክፍፍል እንዳይዳብር በማድረግ ህብረተሰቡን የሚያስተሳስር የውስጥ ገበያ እንዳይስፋፋ ማገድ ፣ በዕቅድ የሚሰራ ከተማና መንደር እንዳይካሄድ እንቅፋት መሆን ፣ ወይም የከተማዎችን በውበት መሰራት ዕውቀት አለመኖር ፣ ሰፊው ህዝብ በደሳሳ ጎጆና በጭቃ ቤት በተሰራ የቆርቆሮ ቤት እንዲኖር እንዲገደድ በማድረግ የህብረተሰቡን የማሰብ ኃይል እንዳይዳብር ማገድ...ወዘተ. የአገዛዙ ዋና ባህርዮች ናቸው። ባጭሩ የአገዛዙ ተልዕኮ ጥፋት እንጂ ሶሻሊስት ወይም አብዮታዊ ዲሞክራት ስለሆነ አይደለም እንደዚህ ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚከተለው። የተቅዋም የነጻ ገበያ ፖሊሲ ከሶሻሊስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር በፍጹም ሊጣጣም አይችልም። የውጭውን ገንዘብ ከዶላር ጋር ሲወዳደር ዝቅ ማድረግ ሶሻሊስታዊ ፖሊሲ ነው ሊያሰኝ የሚችል አይደለም። በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበሩትን ኩባንያዎች ለግል ባለሀብቶች መሸብሸብና ጥቂቱን ማደለብ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና በፍጹም ሊሆን አይችልም። የአገርን ገበያ ከውጭ ለሚመጣ ዕቃ ክፍት አድርጎ ያሉት ኢንዱስትሪዎች እንዲዳከሙ ማድረግ ከሶሻሊሰት ኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር ሊጣጣም የሚችል አይደለም። መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ብቻ ስላደረገ ኮሙኒስታዊ የሚያሰኘው ነገር የለም። ዛሬ የፈለጋችሁትን አድርጉ ብሎ መሬትን ለውጭ ከበርቴዎች እየቸበቸበና የባርነት ስራ እንዲሰፋፋ እያደረገ ነው። ታዲያ ምኑ ላይ ወያኔ የአብዮታዊ ዲሞክራሲዊ ፖሊሲ ነው የሚያካሂደው እያልን አጉል ቅስቀሳ የምናደርገው? የተቅዋም ፖሊሲን(Structural Adjustment Program) በሚመለከት በብዙ የአፍሪቃ አገሮች በሌላ መልክ ይካሄዳል። አንዳንዶች እንደሚሉት እንደዚህ ዐይነቱን ፖሊሲ መከተል የጥቁር ህዝብ ባህርይ እየሆነ መጥቷል። የሚሰራውን የማያውቅና እንደ አሽከር የሚታዘዝ ለማለት ነው። ይህ በጥቂቱ ትክክል ቢሆንም ዋናው ችግር ግን በአፍሪቃ ውስጥ የባህል አብዮት ወይም ሬናሳንስ ስላልተካሄደና በዚያውም መጠንም የተዘበራረቀ ትምህርት በመግባቱ የአስተሳሰብ መዘበራረቅ ሊፈጠር ችሏል። በኔ ግምት የዛሬውን የአገራችንን ሁኔታና አገዛዙ የሚከተለውን ፖሊሲ ከፍልስፍናና ከህሊና ሳይንስ አኳያ መመርመሩ ለችግሩ መፍትሄ ሊሰጠን ይችላል ብዬ አምናለሁ። ችግሩ የባህል ጉዳይ ነው። የእነ አቶ መለሰና ተከታዮቻቸው አስተሳሰብ በጠባብ አመለካከት የተቀረጸና ታሪክን ለመስራት የተዘጋጀ ባለመሆኑ የግዴታ እንደዚህ ዐይነቱን የጥፋት ፖለቲካ እንዲከተሉ ተገደዋል። ሁሉን ነገር የሚያዩትና የሚያነቡት በጠላትና በወዳጅ መሀከል በመክፈል ነው። የአስተሳሰብ አድማሳቸው የጠበበ በመሆኑ ሌላው ቢቀር ለልጅ ልጆቻቸው ምን ዐይነት አገር ጥለው እንደሚሄዱ የሚታያቸው አይደሉም። ነገሮችን ሁሉ በጭንቅላታቸው እያቆመ ነው የሚያዩት። የግሪክ ፈላስፎች እንደሚሉት አእምሮአቸው ስለተጋረደ የሚመለከቷቸው ቆሻሻ ነገሮች ሁሉ ቆንጆ መስለው ነው የሚታይዋቸው። ህዝብ ቢራብ ፣ ቢጠማና ቢሰቃይ ደንታቸው አይደለም። ምክንያቱም ጭንቅላታቸው በሰብአዊ ፍልስፍና የተቀረጸ አይደለምና! ይህንን የአገዛዙን ክህደትና አረመኔያዊ አገዛዝ ትተን ትግሉ በአብዮታዊ ዲሞክራቶችና በሊበራል ዲሞክራቶች ነው ብለን በጭፍን የምንታገል ከሆነ እኛም ከእነ አቶ መለስ ባንሰተካከል እንኳ ባነሰ መልክም ቢሆን ድህነትን ፈልፋዮች መሆናችን የማይቀር ይሆናል። በተለይም በአለፉት አምስትና ስድስት ዐመታት ዐይን ለዐይን የተያየን የሊበራል ዲሞክራሲ አራማጆች ይህንን ነው የሚያረጋግጡልኝ። ለውይይት ያልተዘጋጁ ፣ ዕምነታቸውን ከኢትዮጵያዊ ይልቅ በፈረንጅ ላይ የጣሉ! ይህም የሚያመለክተው ትልቅ በጭንቅላት ውስጥ የተቀረቀረ የባህል ግድግዳ እንዳለ ነው። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት የሊበራል ዲሞክራቶችን ሎጂክ ደግሞ ልመርምር።

## የሊበራል ዲሞክራሲ ሎጂክና ችግር!

በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ ደርጅት ይህንን ርዕዮተ-ዓለም እከተላለሁ ብሎ ለመታገል ሲነሳና የዚህኛውን ወይም የዚያኛውን የውጭ ኃይል ቡራኬ ለማግኘት ሲጣደፍ ህዝባችን ውክልና ስለሰጠው አይደለም። በዚህ ርዕዮተ-ዓለም ብቻ ነጻ ታወጣኛለህ ብሎ ተመራምሮ በመድረስ ኃላፊነት ስለሰጠው አይደለም። ይህንን ወይም ያኛውን ርዕዮተ-ዓለም የመከተል ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄና ችግር አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝቦች መሰረታዊ ጥያቄ ሰላም ማስፈን ፣አገርን ከድህነትና ከረሃብ ማላቀቅ ፣ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት ፣ ነፃነትና ብሄራዊ ክብርን ማስጠበቅ ፣ በአገሩ ውስጥ መከበርናና ለውጭ ኃይል ታዛዥ ያልሆነ አገዛዝን ማየት። ባጭሩ ህዝባችን የሚሻው ብልጽግናን የሚያመጣለትን አገር ወዳድ አገዛዝ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በርዕዮተ-ዓለም

ስም የሚነግዱበትን ማንኛውንም ኃይል አይፈልግም። የተለያዩ ድርጅቶችም ይህንን ወይም ያኛውን ርዕዮተ-ዓለም ይዘው እዚህና እዚያ ቢሉ ለማየት የሚፈልገው ምኞቱ እንዲመነዘርለት ብቻ ነው። ህልሙ ዕውን እንዲሆንለት ነው። ህዝባችን የሚሻው በማቴሪያልና በህሊና መረጋጋት ሊለካ የሚችል መልስ ነው።

ያም ሆነ ይህ አንድ ወጥመድ ውስጥ የገባን ይመስለኛል። ርዕዮተ-ዓለም እንደመለኪያና መነገጃያ እንዲያም ሲል ህዝብን ማታለያ በሆነ ዐለም ውስጥ ነው የምንገኘው። ለጊዜውም ቢሆን የምናመልጠው ጉዳይ አይደለም። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በእርግጥስ የኢትዮጵያን የተወሳሰበ ችግር በሊበራል ዲሞክራሲ ርዕይ መፍታት ይቻላል ወይ? ችግሩንም በዚህ ፍልስፍና መግለጽና መተንተን ይቻላል ወይ? ደርጅቶችስ ምን ያህል በርዕዮተ-ዓለሙ ያምናሉ? በእኔ ዕምነት እነዚህን ጥያቄዎች የማያቀርብና መልስ ለመስጠት የማይሞክር ለችግሩ መፍትሄ ይሰጣል ብዬ አላምንም።

የሊበራል ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ምድር ተግባራዊ መደረግ አለበት ሲባል በዙ ነገሮች በጭንቅላት ውስጥ መቋጠር አለባቸው። በመጀመሪያ ድረጃ የሊበራል ዲሞክራሲ በግለሰብአዊ ድርጊትነትና ነጻነት ያምናል ፤ አምባገነንነትን ይቃወማል። ይህንን ፍልስፍና በተቀበለው ድርጅት ውስጥ የሃሳብ መንሸራሸር መኖር አለበት። በሶስተኛ ደረጃ የካድሬ ፖለቲካን ይቃወማል። የፓርቲው አመራርም ሆነ ወደ ታች ያሉ አባሎች የጭንቅላት ነጻነት የሚሰማቸውና ለሚያምኑበት ርዕይ የሚታገሉ መሆን አለባቸው። በአራተኛ ደረጃ ሊበራል ዲሞክራት ነኝ የሚል የሌላውንም ፓርቲ ነጻነትና መብት ማወቅ አለበት። ተወዳዳሪ መሆን አለበት። አምስተኛ ፣ ሊበራል ዲሞክራሲ ህዝባዊ ተሳትፎን(Participatory Democracy) አይቀበልም። ሁሉንም ነገር የሚደነግጉትና ተግባራዊ የሚያደርጉት ውክልናን አግኝተናል የሚሉት ናቸው። ይህም ማለት በተዘዋዋሪ የኤሊት አምባገነንነት ይፈጠራል ማለት ነው። ወደ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመጣ ሁሉ ነገር ከነጻ ገበያ ሎጂክ አንጻር መነደፍ አለበት። የግል ሀብት መሬትንም ጨምሮ ግላዊ ብቻ ሳይሆን የሚሸጥና የሚለወጥም መሆን አለበት። በሊበራል ዲሞክራቶች ዕምነት ህብረሰተብአዊ ችግሮች በሙሉ የሚፈቱት በረቀቀ የገበያ ኃይል ነው። የመንግስት ጣልቃ ገብነት መኖር የለበትም። መንግስት በአንዳች ዐይነት የሞኔተሪም ሆነ የፊስካል ፖሊሲ ኢኮኖሚውን ለማረም ሽር ጉድ ማለት የለበትም። ሁሉም ነገር ለገበያው በመተው ገበያ እንዲፈታው ይደረጋል። በሊበራል ዲሞክራቶች ዕምነት ከቀረጥ ጀምሮ እሰከ ድኅማና አገርን እስከመገንባት ያለው ሂደት ለገበያው መተው አለበት። አሁን በያዝነው ዓለም ደግሞ ገንዘብ ያለው ብቻ ሁሉንም ነገር ማድረግ ስለሚችል በተለይም እንደመሬት የመሳሰሉት በጥቂት ሀብታሞች ቁጥጥር ስር እየዋሉ በመምጣት ሰፊው ህዝብ እንዲገፋ ይገደዳል። ሰፊው ህዝብ በትንሽም ቢሆን ራሱ ቤት ሰርቶ የጓሮ አትክልት እየተከለ እንዳይኖር ይፈረድበታል። ዛሬ በብዙ የካፒታሊስት አገሮች ያለው ችግር ኢንቬስተርስ የሚባሉ ሰፊውን ህዝብ ከመሀል ከተማ እየገፉና ትላልቅ ፎቅ ቤቶች እየሰሩ ነው። ልቅ ነጻ ገበያ የግዴታ ሰፊውን ህዝብ በማግለል የሚካሄድ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ነው። ወደድንም ጠላንም እንደዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ተግባራዊ ሲሆን ወደ አናርኪዝም ያመራናል። እንዴት?

እኔ አስከማውቀው ድረስ በካፒታሊዝም የአኪኖሚ ዕድገት ውስጥ የሊበራሊዝም ፍልስፍና የተጸነሰውና እያደገ የመጣው ካፒታሊዝም በመርካንትሊዝም ፍልስፍናና የኢኮኖሚ ፖሊሲ መልክ እያያዘ ከመጣ በኋላ ነው። የከበርቴው መደብ በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በመንግስትም ደረጃና በባህል አሸናፊነትን እየተቀዳጀ ከመጣ በኋላ ነው። ስርዓቱ በብዝበዛ ላይ ይመስረት አይመስረት ራሱን የቻለ ታሪክ ነው። ለማንኛውም የነጻ ገበያ በንጹህ መልኩ በእንግሊዝ አገር በስራ ላይ ለጥቂት ዐመታት ከዋለ በኋላ ብዙ ህብረተሰብአዊ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ስለተፈጠሩና ድህነትም ስለተስፋፋ የግዴታ የድህነት ህግን በማውጣት ችግሩን ለመቅረፍ መንግስት መሯሯጥ ተያያዘ። የነጻ ገበያን በሚመለከት በእንግሊዝ የኢኮኖሚ ምሁራን ዘንድ ክርክር ያመጣና እኛ ዛሬ እንደምንተረጉመው ዐይነት ሳይሆን ፣ ሁሉም የነጻ ገበያ አፍላቂዎች ነገሩ በዚህ ሊቀጥል እንደማይችል በመገንዘብ ዕርማት እንዲደረግ እስከመታገል ደርሰዋል። በፈረንሳይና በጀርመን የተካሄደውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመለከት የኢንዱስትሪ አብዮት ያስፈልጋል በሚል በተለይም ኮልበርት የመርካንታሊዝምን ፖሊሲ በመከተል ወደ ወስጥ ሰፊ ገበያ እንዲዳብር መሰረት የጣለበት ሁኔታ ይታወቃል። በጀርመንም ነጻ ገበያ በንጹህ መልኩ በተግባር የዋለበት ጊዜ የለም። በዕውቅ አማካይነት ነው ጀርመን በአጭር ጊዜ ውስጥ የተወሳሰበ ኢኮኖሚ ልትገነባና በቴክኖሎጂ ልትመነጥቅ የቻለቸው። ወደ ስዊድንም ስንመጣ በነጻ ገበያ ፖሊሲና ፍልስፍና የተስተካከለ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት ስለማይቻልና ህብረተሰብአዊ መረጋጋት እንደማያስከትል ስለታመነበት በፕሮፌሰር ጉናር ምይራዳል አማካይነት በመንግስት የተደገፈ ፖሊሲና ኢንስቲቱሽናዊ ሪፎርም ተግባራዊ በማድረግ ዛሬ የምናያትን የበለጸገች ስዊድንን መገንባት ተችሏል።

በአጭሩ ዛሬ በለጸጉ በሚባሉ አገሮች ሁሉ ውይይት ሳይካሄድና ዕምነት ሳይኖር ጥቂት እናውቃለን የሚሉ ምሁራን በህዝቦቻቸው ላይ የጫኑት ፖሊሲ እንደሌለ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ታሪክ ላጠናና ላገላበጠ በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል። ባለፈው በእንገሊዘኛ ባወጣሁት „ The Great Confusion“ በሚለው ጽሁፌ ላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ፣ ነገሩ እጅግ የተወሳሰበና እንደዚህ በነጻ ገበያ ሎጂክ ብቻ መታየት እንደሌለበት ነው። የብዙዎቹ የኛ አገር የነጻ ገበያና የሊበራል ዲሞክረሲ አፍቃሪዎች ችግር የካፒታሊዝምን ዕድገትና ውስብስብ ሂደት በደንብ ለመገንዘብ ያለመቻል ነው። ከተራ የኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም ሎጂክ በመነሳትና ህብረተሰብን የመገበያያ መድረክ ብቻ አድርጎ በመገመት ሁሉም ነገር ለገበያው ቢለቀቅ ተዓምር እንደሚፈጠር ሊያሳምኑን ይሞክራሉ። ከእነ አቶ ኃይሉ ሻውል ፓርቲ አንስቶ እስከ ግንቦት ሰባት ድረስ ያለው መምታት የሚያረጋግጠው በነጻ ገበያና አገርን በመገንባት መሀከል የእሳትና የጭድ ዐይነት ሁኔታ እንዳለ ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት ያለመቻል ነው። ሁሉም ነገር ለገበያው መለቀቅ አለበት ካልን ልንቆጣጠረው የማንችለው የድረግ ካርቴሎች የሚቆጣጠሩት እንደሚክሲኮ ፣ ብራዚል ወይም እንደ አርጀንቲና በፍጹም ጤናማ ህዝብን የሚጠቅም ፖሊሲን ለመውሰድ የማያስችል ሁኔታ በመፍጠር ዘለዓለማዊ የህብረተሰብ መመሰቃቀል እንዲፈጠር እናደርጋለን። እህአዴግን ስለምንጠላ ወይም ደግሞ የእነ አይም ኤፍናና የአሜሪካንን ቡራኬ ለማግኘት ስንል በአወቅሁኝ ባይነት በስሜት ብቻ እየተገፋፋን ተግባራዊ ለማድረግ የምንሞክረው ፖሊሲ ኢትዮጵያችንን እንድናጠፋ የሚጋብዝ እንጂ አዲስና የተከበረች አገርን እንድንገነባ የሚያስችለን አይደለም። በነጻ ገበያ ፍልስፍና አማካይነት አንድ አገር ጠንካራ ሆና የተገነባችበት ጊዜ በታሪክ ታይቶ አይታወቅም። ብሄራዊ ነጻነቷ የተከበረችና በቴክኖሎጂ የመነጠቀች አገር ልትገነባ የምትችለው በነጻ ገበያ ፍልስፍና እንዳልሆነ ሺህ በሺህ የሚቆጠሩ መጽሀፍን ላገላበጠ ማረጋገጫ ሊያገኝ ይችላል። በተጨማሪም ለነጻ ገበያ መታገል ማለት ለህብረተሰብ ዕድገት መታገል እንዳልሆነ ቢያንስ ያለፈው የስድሳ ዐመት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ታሪክ ያረጋግጣል። ለህብረተሰብ ዕድገት በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ቢያስፈልግም ፣ ዋናው ዓላማ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሳይሆን እንዴት አድርጎ አንድ በባህል የመነጠቀና የተረጋጋ ህብረተሰብ መመስረት ይቻላል የሚለው መሰረተ-ሃሳብ ነው እስከ አስራዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ ፈላሳፋዎችንና የህብረተሰብ ሳይንስ ምሁራንን ሲያከራክር የከረመው። በሃያኛውና በሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን ግን እየተስፋፋና እንደ ኤድስ በሽታ የዓለምን ማህበረሰብ ያዳረሰው ጭፍን አስተሳሰብ ህብረተሰብአዊ ዕድገትን በሳይንስ ላይ ከተመሰረተ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ነጥሎ ማየትና ሁሉንም እንቅስቃሴ ወደ ንግድና ወደ ገንዘብ ማካበት ቀንሶ ማየት ነው። ወደ አገራችንም ስንመጣ አንዳንድ ወጣት ኢኮኖሚስቶች የሚያካሂዱት ቅስቀሳ የፍልስፍና መሰረት የሌለው ብቻ ሳይሆን እጅግ አደገኛና ህብረተሰብአዊ ትርምስን የሚፈጥር አካሄድ ነው የሚስተጋባው። እነዚህ ጎልማሶች የታወቁ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ጠጋ እያሉ የሚያደርጉት የነጻ ገበያ ልፈፋ በመሰረቱ የካፒታሊዝምን ዕድገት የሚቀናቀን ብቻ ሳይሆን አገርንም የሚያፈራርስ ነው። የቴክኖሎጂና የሳይንስ አብዮት እንዳይካሄድ እንቅፋት የሚሆን ነው። እነዚህን የመሳሰሉት ስልጣን ከያዙ እንደ ዛሬው አገዛዝ ከአይ ኤምፍ ትዕዛዝ እየተቀበሉ የሞኔተሪና የፊስካል ፖሊሲ እያሉ በማደናበርና ህዝቡን ግራ በማጋባት ድህነትን እንደሚያስፋፉ ካሁኑ መታወቅ አለበት።

የነጻ ገበያና የሊበራል ዲሞክራሲ ርዕይ ወገናዊ እንጂ ህዝባዊና አገራዊ ርዕይ የለውም። ከአንድ መደብ ጋር የሚቆራኝ ርዕይና ፖሊሲ እንጂ ከታች ወደ ላይ ቀስ በቀስ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያካትት ፖሊሲ አይደለም። በግለሰብአዊ ድርጊት ላይ ብቻ በማትኮርና ሁሉም ነገር በረቀቀው የገበያ ዘዴ ይፈታል በማለት በሚሊዮን ተደርድሮ የሚገኘውን የህብረተሰብአችንን ችግር በህብረተሰብአዊ ፣ በመንግስትና በግለሰብ የተባበረ ድርጊት እንዳይፈታ የሚያደርግ አደገኛ አዝማሚያ ነው። ልክ እንደ አብዮታዊው ዲሞክራሲ ወገናዊ በመሆን ከህብረተሰብአዊ ስምምነት ይልቅ ህብረተሰብአዊ ፍጥጫን የሚያመጣ ነው። የዛሬው አገዛዝ በጉልበት እንዳደረገው ሁሉ ፣ የሊበራል ዲሞክራቶች ነን ባዮች ደግሞ በንጹህ የገበያ ሎጂክና ፖሊሲ በመታገዝ ሁሉም እንደፈለገው መወዳደር ይችላል በሚል ገበያውን ልቅ በማድረግ የተወሰነው ህብረተሰብ ክፍል የሚደልብበት ፣ ሌላው ደግሞ ወደ ድህነት ዓለም የሚገፈተርበት ሁኔታ መፍጠር ነው። ፓሊሲው ፀረ-ካፒታሊዝምና ጠንካራ የኢንዱስትሪ ከበርቴ መደብ እንዳያድግ የሚያግድ ነው። ጠንካራና እርስ በርሱ የተሳሰረ ህብረተሰብ እንዳይገነባ እንቅፋት የሚሆን ፍልስፍና ነው።

በእርግጥ ሁሉም ለነጻ ገበያ እንታገላለን የሚሉ ድርጅቶች ፍላጎት ይህ እንዳደለ ይገባኛል። የተከበረች ኢትዮጵያንም ይመኙ ይሆናል። ችግሩ ግን በአወቅሁኝ ባይነትና በስሜት የሚወሰዱ ፖሊሲዎች ያልገመትነው ሁኔታ ውስጥ ነው የሚከቱን። ለምሳሌ የየካቲቱ አብዮት ጠንሳሾችና ታጋዮች እንደዚህ ዐይነቷ ኢትዮጵያ ትፈጠራለች ብለው በህልማቸውም ሆነ በዕውናቸው እንዳላሰቡ በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። መደማመጥ

ስላልቻሉ ፣ አንዱ አንዱን ይንቅ ስለነበር ፣ አንዳንዶችን እልከኝነትና ትቢተኝነት ያጠቃቸው ስለነበር ፣ እንዲሁም ደግሞ ዓለም አቀፋዊውን የፖለቲካ አወቃቀር በቅጡ ለመገንዘብ ካለመቻል የተነሳ ያላሰቡት ሁኔታ ውስጥ ገቡ። ይህን የመሰለ ፖለቲካ ዛሬም በግልጽ ሲካሄድ ይታያል። ለመወያየት አለመዘጋጀት ፣ ሌላውን አለማመንና በጥርጣሬ ማየት ፣ ፖለቲካን በተሸናፊና በአሸናፊ መሀከል የሚደረግ ትግል አድርጎ መውሰድና ቡድናዊ ስሜትን አዳብሮ ሌላውን ለማጥቃት መሞከር የምናየው ነው። ለህብረተሰብ ግንባታ እንደዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ መርዝ ነው። የኛ ትልቁ ችግር ማንነታችንን ሳንረዳ ሊበራሎች ነን ብለን ለመመጻደቅ መሞከር ነው። ብንሆን ጥሩ ነው።ደስታውን አልችለውም። ከብዙዎቹ ፊትና አስተሳሰብ የማነበው ግን ልፈፋና ተግባር እንደማይጣጣሙ ነው።

በእልክ እስካልሆነ ድረስ የአንድ አገር የኢኮኖሚም ሆነ የማህበራዊ ፖሊሲ በአንድ ድርጅት ወይም ጥቂት ግለሰቦች አዋቂነት ሊወሰን የሚችል መሆን የለበትም። እኔ ስልጣን ከያዝኩ ይህንን ፖሊሲ እከተላለሁ ማለት የታሪክን ሂደት አለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን አንድ ህብረተሰብ እንዴት እንደሚገነባ ለመረዳት አለመጣር ነው። በመጀመሪያ የፈለገው ኃይል የፈለገውን ስም ይዞ በአሸናፊነት ስልጣን ላይ ቁጥጥ ቢል ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ፖሊሲዎች በሙሉ ሰፊው ህዝብና በፓርላሜንት ውስጥ ውክልናን አግኝተው የተቀመጡት አጽድቀው የተቀበሉትን ህገ-መንግስት በመመርኮዝ ብቻ ነው። አንድ ፓርቲ ህገ-መንግሰት ላይ የሰፈረውን አንቀጾች ሽሮ እኔ በዚህ ፖሊሲ ነው የምመራው ብሎ ቢመጻደቅና አገር አፍራሽ ፖሊሲ ቢወስድ እንደ አምባገነናዊነት ነው የሚቆጠረው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ አንድ ህዝባዊ ተቀባይነት ያገኘ ህገ-መንግስት አንድን ህብረተሰብ የሚመለከት ፣ ከዜግነት መብት እስከ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና እንደዚሁም ደግሞ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ፓሊሲ እንዲሁም የብሄራዊ ነጻነትን ጥያቄ ያካተተ ሰፊ ህግ መሆን አለበት። በጥቂት ሃሳቦች ላይ ብቻ የተመረኮዘ ከሆነ ሁሉም በየፊናው እየተነሳ እኔ ስልጣን ከያዝኩ መሬትን ግላዊ አደርጋለሁ ፣ የዓለም አቀፋዊ ህግን በመከተል የአነ አይ ኤም ኤፍን ፖሊሲ ተግባራዊ አደርጋለሁ ፣ለአሜሪካን የጦር መስፈሪያ መሬት ሰጥቼ ከዚያ እየተነሳ ሌሎች አገሮችን እንዲወር አደርጋለሁ እያለ ሊዘላብድ ይችላል። እንደዚህ ዐይነቱ አካሄድ ለአገር ግንባታ የማያመች ብቻ ሳይሆን ልዕልናን በማስደፈር ማንም እየመጣ የሚፈነጭበት አገር እንዲሆን ይሆናል ማለት ነው። ባህልና ታሪክ እያልን የምንጮህለት መፈክር ሁሉ መሬት ላይ እንደፈሰሰ ውሃ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህም አብዮታዊ ዲሞክራሲ በሉት የነጻ ገበያ ሌላም ሌላ ጥቂቶች ከህገ-መንግስት ውጭ አልፈው የራሳቸውን ቅዠት ተግባራዊ ለማድረግ ከሚሯሯጡበት የሚያልፍ አይሆንም።አንድ ህገ-መንግስት ፍልስፍናዊ ፣ታሪካዊ ፣ባህላዊ ፣ስነ-ልቦናዊና እንዲሁም ደግሞ የተፈጥሮን ሀብት የሚንከባከብና ጠቅላላውን ህብረተሰብ የሚጠቅም የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሊንጸባረቅበት የሚችልና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መሆን አለበት። በብዘዎቹ ፓርቲዎች ዘንድ በፓርቲ ፕሮግራምና በህገ-መንግስት መሀከል ያለው ዲያሌክታዊ ግኑኝነት ግልጽ የሆነ አይመስለኝም። የህገ-መንግሰት ምንነት ሲታወቅና ይህ ደግሞ ሰፋ ባለመልክ ተዘጋጅቶ ማንኛውም ፓርቲ ፕሮግራሙና ህገ-መንግስቱን በማያዛንፍ መልክ የሚነድፍ ከሆነ በእርግጥም ዲሞክራሲያዊ ባህል የገባው ብቻ ሳይሆን ለአገር ዕድገት ሊታገል የሚችል ነው ብለን ልንቀበለውና ልንደግፈው ይገባል። የማየው ፣ የማነበውና የሚደረገውም ትግል ይህንን ያገናዘበ ሳይሆን ሁሉም እንደፈለገው በሊበራሊዝምና በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስም እየተመጻደቀ ልቅ ስርዓት እንዲመሰረት በማድረግ የአገር ህልውና ደብዛው እንዲጠፋ የሚደረግ ትግል ነው የሚመስለው።በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠሩ ማሰብ የሚችሉ ሰዎች የሚገነቡት አገር አይሆንም ማለት ነው። ይህንን ለመረዳት ችግሩን ከሌላ አኳያ ማየት የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

## ችግራችን ታዲያ ከምኑ ላይ ነው ?

ከላይ አለፍ አለፍ ብዬ ለማሳየት እንደሞከርኩት የአገራችን መሰረታዊ ችግር የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ችግር አይደለም። ችግሩም በሊበራል ዲሞክራሲና በነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሊፈታ የሚችል አይደለም። የአገራችን ዋናውና መሰረታዊው ችግር የባህል ጉዳይ ነው። የአንድን ህብረተሰብ ሁኔታ በሰፊው ከሁሉም አቅጣጫና በጥልቀት ማየት ባለመቻል በራስ ጥቅም ብቻ በመታለል የዛሬን ብቻ እያሰቡ የታሪክን ሂደት መዘንጋትና ታሪክን ለመስራት ባለመቻል ዛሬ ብቻ ኑሮ ለመሞት የሚደረግ የሞት የሽረት ትንንቅ ነው። የዛሬው አገዛዝ ድርጊት አርቆ ካለመሰብ የመነጨ ፣ በእልከኝነትና በአወቅኹኝ ባይነት የሚዘባነን ግን ደግሞ የሚውስዳቸውን ድርጊቶች በፍጹም ሊያገናዝብ

የሚችል አይደለም። ለምሳሌ ትግሬንና ኤርትራን አንድ ላይ አጣምሮ `ጠንካራ የኢንዱስትሪ` አገር እመሰረታለሁ የሚለው ግምት በፍጹም ስለ ኢኮኖሚ ዕደገትና ሎጂክ በቅጡ አለመረዳት ነው። ካፒታሊዝም ወይም በዘመኑ አነጋገር የገበያ ኢኮኖሚ ሰፊ ገበያ ያስፈልገዋል። ካፒታልና ሰራተኛ እንዲሁም ሌሎች ሀብቶች በቀላሉ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። በተጨማሪም ለገበያ ኢኮኖሚ ወይም ለካፒታሊዝም ተግባራዊነት የሰፊው ህዝብ የመግዛት ኃይል በየጊዜው ማደግ አለበት። የሚመረት ዕቃ መሸጥ አለበት። በገንዘብና በዕቃ መሀከል ያለው ግኑኝነት እየጠበቀ ሲሄድ የካፒታል ክምችት ይዳብራል። ገንዘብ በፍጥነት ሲሽከረከር ህብረተሰብአዊ ከመሆን አልፎ ወደ ካፒታልነት ይቀየራል። የእነ አቶ መለስ ጭፍን አስተሳሰብ የጥሬ ሀብት ደሃ በሆኑት ትግሬና ኤርትራ ውሰጥ ከላይኛው ግምት ውጭ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን አመጣለሁ ማለት የኢኮኖሚ ውስጣዊ ህግን አለማወቅ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ቅዠትም ነው። ረጋ ብለን ብንመረምር የዛሬው አገዛዝ በአለፉት አስራዘጠኝ ዐመታት የወሰዳቸው ፖሊሲዎች በሙሉ ከማሰብ ድክመት የፈለቁ ናቸው። በይዘታቸው ከሌሎች የአፍሪቃ አገሮች የሚለዩ አይደለም። ልዩነቱ የዛሬው አገዛዝ የወሰዳቸውና የሚወስዳቸው ፖሊሲዎች በሙሉ በእልክ ላይ የተመሰረቱና ግልጽ መሆናቸው ነው።

ከዚህ ስንነሳ በአገራችን የባህል አብዮት ወይም ሰፊ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ባለመካሄዱና አስተሳሰባችንም በጠባቡ ስለተቀረጸ የሚሰሩት ስራዎች በሙሉ ወደ አገር አፍራሽነት የሚያመሩ ናቸው። ስለሆነም የዛሬውን አገዛዝ በምርጫ ወይም በአንዳች ነገር መጣሉ ብቻ አይበቃም። በአገራችን ምድር ዘለዓለማዊ ሰላም እንዲመጣ ከተፈለገ ከነጻ ገበያና ከሊበራል ዲሞክራሲ ባሻገር አልፈን ማየት አለብን። ውይይታችን ፍልስፍናዊ ፣ህብረተሰብአዊ ፣ህሊናዊና ታሪካዊ መሆን አለባቸው። በተወሰኑ ነገሮችና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንድናተኩር የሚያደርጉን መሆን የለባቸውም። በተጨማሪም በአገራችን የሚካሄደውን የተመሰቃቀለ ሁኔታና በውጭው ዓለም ያለውን መተሳሰር በግልጽ መወያየት ያሰፈልጋል። እንደማየው ከሆነ በአንዳች ፍርሃት የተዋጥን ይመስለል። በአገራችን ምድር የሚሰራው ወንጀል ሁሉ በአገዛዙ ብቻ እንደሚካሄድ በመቁጠር የውጭ ኃይሎች አገርን የማፈራረስ ሚና ለመመልከትና ለመመራመር ዝግጁ አይደለንም። በእርግጥ አንዳንድ ግለሰቦችንና ፓርቲዎችን ካለባቸው ፍቅር ማላቀቅ አይቻልም። በሌላ ወገን በፈለገው ስም የሚካሄድ ትግልና ቅስቀሳ የብሄራዊ ነጻነትን ጥያቄ አሳንሶ ማየት የለበትም። በአሜሪካና በኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ የእሴት አንድነት ወይም ተመሳሳይነት የለም። የኢትዮጵያ ህዝቦች የራሳቸውን ታሪክና ባህል ማዳበር ይፈልጋሉ። እንደዚሁም ከማንኛውም አገር ለዕድገታቸው የሚያመቻቸውን የአስራር ስልትና ባህል ሊወስዱና ከባህላቸው ጋር ሊያዋህዱ ይችላሉ። አገርን የሚጠቅም ፣ ዕድገትን የሚያፋጥን የአሰራር ስልትና ባህል በማንኛውም አርቆ አሳቢ ምሁር የሚደገፍ ነው። በሌላ ወገን ግን በታሪክ እንደታየውና የብዙ አገሮችም ልምድ እንደሚያስተምረን በተለይም ከአሜሪካ ጋር የጠበቀ ግኑኝነት የመሰረቱ አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት የማይታይባቸው አገሮች ብቻ ሳይሆኑ በባህልም እየተከሰከሱና ህዝቦቻቸውም የአገር መለያቸውን እያጡ ነው። ከኤልሳልቫዶር እስከ ጓዋቴማላ ያሉ አገሮች ከአሜሪካን በመጡ ጋንግስተሮችና የሚሊተሬ ያሰራር ስልት እየተሰቃዩ ነው። የአሜሪካንም ስትራቴጂ በየአገሮች ውስጥ ጥቂቶችን ማደለብና ሰፊውን ህዝብ ደግሞ የማሰብ ኃይሉ እንዳያድግና በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ እንዳይገነባ ማድረግ ነው። ስለዚህም ትግላችን በአገዛዙና በውጭ ኃይሎች መሀከል ያለውን መተሳሰርና መደጋገፍ ማጥናትና መዋጋት መሆን አለበት። የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ የነገሮችን ውስብስብነት እንድናይ የሚጋብዝ ነው። ኢህአዴግ ቢወገድ አንድ ትንሽ ድል መቀዳጀት ይቻል ይሆናል። ሙሉ ድልን መጎናጸፍ የምንችለው ግን ጠለቅ ወዳለ ሁኔታ ስንሄድና ከራሳችን በስተቀር ራሳችንን ማንም ነጻ ማውጣት እንደማይችል ስንገነዘብ ብቻ ነው። ቻይናዎች ራሳቸውን በራሳቸው ኃይል ነው ነጻ ያወጡት። አሜሪካንን ወይንም የምዕራቡን ዓለም በመለማመጥና በመማጸን አይደለም። ስለዚህም የኛ ትግል ራስን መቻል ፣ በማንም የውጭ ኃይል አለመተማመን የሚለውን መሰረተ-ሃሳብ በጭንቅላት የቋጠረ መሆን አለበት። ማንኛውም አገር ወዳጅ የለውም። ይህንን አለመረዳት በዓለም አቀፍ ላይ የሚካሄደውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፉክክርና የበላይነትን ለመቀዳጀት የሚደረገውን ሩጫ ለመገንዘብ እንዳለመፈለግ ይቆጠራል። የጀርመኑ ቻንስለር ቢስማርክ እንዳለው በሁለት አገሮች መሀከል የሚኖረው ግኑኝነት በጥቅም ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው። በፍቅር ላይ የተመሰረተ ግኑኝነት በታሪክ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም።

ይህ የባህል ችግር ፣ የነገሮችን ምንነት ከሁሉም አቅጣጫ ለማየትና ለመመርመር አለመቻል እየመላለሰ ተራ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲከተን ይታል። ተግባራችን ሁሉ ኮፖለቲካል አክቲቪዝም ሊያልፍ የሚችል አልሆነም። በየጊዜው ብቅና ጥልቅ የሚል ነው። በየቦታው በቡድን በቡድን እየተገናኙ ወይም እየተደራጁ ለአገር

**ግንባታ በሚጠቅሙ ነገሮች ላይ ለማጥናትና መፍትሄ ለመፈለግ ዝግጁነት የለም። ሁሉም ነገር የታወቀ ነው በሚል አጉል አባባል ነገሮችን አድበስብሶ ማለፍ የተለመደ ነገር ሆኗል። የፖለቲካ መሪዎች ነን የሚሉት ደግሞ አባሎቻቸው ጥናት እንዲያጠኑ መመሪያ ሲሰጡ አይታይም። ከዚህ በተረፈ በሁሉም የዕውቀት ዘርፍ አውቶሪቲ ባለመኖሩ ሁሉም በየፊናው እንደፈለገው ይጽፋል። ለምሳሌ በጀርመን አገር በ19ኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻ ማክስ ዌበር በሶሲዮሎጂ አውቶሪቲ ነበር። በኢኮኖሚክስ፣ በአርክቴክቸርና በከተማ ግንባታ፣ በእርሻና በባዮሎጂ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች አውቶሪቲዎች ነበሩ። የሚጻፉትም ጽሁፎች ተከታታይነት ብቻ ያላቸው ሳይሆኑ ወደ ተግባርም የሚመነዘሩ ነበሩ። እንደዚህ ዐይነቱ የምርምርና የአሰራር ስልት በአገራችን የተለመደ አይደለም። ሁሉም ፖለቲከኛና ፖለቲካን ለማኘክ የሚፈልግ ነው። በዚህ ዐይነት የትግል ስልት እንዴት አድርገን ከገባንበት ማጥ ልንወጣ እንችላለን? ያለው አማራጭ የባህል አብዮት ማድረግ ብቻ ነው። አስተሳሰባችንን ስንለውጥ ብቻ ለአገር ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ እንችላለን።**


**ፈቃዱ በቀለ**

**fekadubekele@gmx.de**


**ማሳሳቢያ**:- **በአገራችን ትችትና መተቻቸት የተለመደ አይደለም። እንደሚታወቀው በአውሮፓ የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ትችት ከፍተኛ ቦታን ይይዛል።ኢማኑ ኤል ካንት የሚባለው ፈላስፋ አንድ ህብረተሰብ አስቸጋሪ ከሆነ ወይም ለለውጥ ዝግጁ ካልሆነ በትች ክርን መደቆስ አለበት ይላል። ህብረተሰብአዊ ጥያቄዎች በሙሉ በግልጽ ለውይይት መቅረብና መፈተን አለባቸው። አንድ ህብረተሰብ ሊያድግ የሚችለው የሚሰራቸውን ስራዎች በየጊዜው ሲመረምርና ሲጠይቅ ብቻ ነው። ለፈጠራ ስራና ለዕድገት ጥያቄ ማቅረብ እጅግ አስፈላጊ ነው። የኋሊት ጉዞ እየተደረገ ጥያቄ ሲቀርብ ለአንድ ችግር ተቀራራቢ መልስ መስጠት ይቻላል። ስለዚህም የዚህ ጽሁፍ ዓላማ በአወቅኹኝ ባይነትና ሌሎች ደግሞ አያውቁም በሚል የተጻፈ አይደለም።ለዲሞክራሲና ተቻችሎ በጋራ አንድ አገር ለመገንባት ዝግጁ የሆነ ማንኛውም ተራ ዜጋ የሚያነሳው ጥያቄ ነው። ስለሆነም ጽሁፉ በንጹህ መንፈስ ቢነበብ አለመግባባትን ሊያስወግድ ይችላል። ከዚህ በተረፈ ከአንድ ወር ተኩል በፊት በእንግሊዘኛ** *“The Great* Confsuion -***The Poverty of Development Economics*”** **በሚል አርእስት በሰፊው የቀረበ ጥናት አለ። በመጨረሻው ላይ የክርክርን አስፈላጊነትና እንደባህል አድርጎ መውሰድ አገርን ለመገንባት የሚጠቅም መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ ይህም ከላይኛው ጋር ተጨምሮ ቢነበብ አለመግባባትን ሊያስወግድ ይችላል ብዬ አምናለሁ።**